*Ethiop.j.lang.cult.commun. June 2026, 11*(1): 223-257

*Bahir Dar University-Faculty of Humanities*
10.20372/ejlcc.v11i1.2953

*ISSN: 2518-2919*

**Research Article** **Open Access**

# The Role of Folk Beliefs in Dejen District Amhara Society

**Anteneh Ayenew** [1*], **Zelalem Teferra** [2] **Solomon Teshome**[3]

[13]Department of Folklore /Culture Studies/, Humanities Faculty, Bahir Dar University, Bahir Dar, PoBox.79, Ethiopia
[2]Department of Social Anthropology, Addis Ababa University, Addis Ababa , Ethiopia

## Abstract

The main objective of this study is to examine and provide a proper analysis of the roles of folk beliefs within the Amhara society of Dejen District. To achieve this objective, data collection was conducted in seven kebeles selected from the total of twenty-four kebeles in the district using purposive sampling techniques. Informants were identified based on factors such as age, climate, lifestyle, gender, and social status. In the process, both snowball and purposive sampling methods were employed as needed. Relevant primary field data were gathered through observation, interviews, and focus group discussions. The collected data were analyzed descriptively using a functional theoretical framework. Accordingly, this study follows a qualitative research design. Finally, the findings reveal that the folk beliefs of the studied society play significant roles in building a healthy society, promoting and preserving religious doctrines, preserving environmental ecosystem, educating ethical behavior, creating psychological relaxeation, promoting humanity, growing the economy, strengthening social cohesion and solidarity, strengthening and sustain culture, building a strong personality, teaching the division of labor, promoting honesty, bringing progress and transition in science and technology, promoting transparency, mutual respect, and accountability.

**ARTICLE HISTORY**
Received: February, 2025
Revised: February, 2026
Accepptted: March, 2026

**Keywords**: *moral, social moral, moral role, practical benefit*

**Citation** Ayenew, A., Getachew, Z. T., & Teshome, S. (2026). The Role of Folk Beliefs in Dejen District Amhara Society . *Ethiopian Journal of Language, Culture and Communication*, *11*(1). 223-257 10.20372/ejlcc.v11i1.2953

**CONTACT:** Anteneh Ayenew , anteayenew@gmail.com

©2026 The Author(s). Published by Faculty of Humanities, Bahir Dar University.
This is an open access article distributed under the terms of the Creative Commons attribution license (http://creativecommons.org/licenses/by/4.0/), which permits unrestricted use, distribution, and reproduction in any medium, provided the original work is properly cited. The terms on which this article has beenpublished allow the posting of the accepted Manuscript in a repository by the author(s) or with their consent.

# የማህበራዊ ግብረገብ ሚና በደጀን ወረዳ አማራ ማህበረሰብ


## አህፅሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደጀን ወረዳ አማራ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ሀገረሰባዊ እምነቶችን ሚና[1] መመርመርና ተገቢ ትንተና ማድረግ ነው፡፡ የጥናቱን ዓላማ ለማሳካትም በወረዳ ውስጥ ከሚገኙ 24 ቀበሌዎች ውስጥ ሰባቱ ቀበሌዎች በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ መረጃ የማሰባሰብ ስራ ተካሂዶባቸዋል፡፡ ማህበረሰቡን በተመለከተ እድሜን፣ አየር ንብረትን፣ የአኗኗር ዘይቤን፣ ጾታን እና ማህበራዊ ደረጃን መሰረት በማድረግ መረጃ አቀባዮችን መለየት የተቻለ ሲሆን፣ በሂደቱ ውስጥ ቅብብሎሽ አስረጅ እና ኢላማዊ የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች እንደ አስፈላጊነታቸው በጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ መሰረታዊና ተገቢ የሆኑ የመስክ መረጃዎች በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ተኮር ውይይት ዘዴዎች አማካኝነት ተሰብስበዋል፡፡ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብን መሰረት በማድረግ ገላጫዊ በሆነ ስልት ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡ ስለሆነም ይህ ጥናት አይነታዊ የምርምር ንድፍን የተከተለ ነው፡፡ በመጨረሻም የተጠኘው ማህበረሰብ ሃገረሰባዊ እምነቶች ጤናማ ማህበረሰብ የመፍጠር፣ ሃይማኖታዊ ዶግማን የማስከበርና የማስቀጠል፣ አካባቢያዊ ስነ-ምህዳርን የማስጠበቅ፣ መልካም ስብዕናን የማስተማር፣ ስነ-ልቡናዊ እረፍትን የመፍጠር፣ የሰብአዊነት ባህርይን የማጎልበት፣ ኢኮኖሚን የማሳደግ፣ ማህበራዊ አንድነትና ትስስር እንዲጠነክር የማድረግ፣ ባህልን የማጽናትና የማስቀጠል፣ ጠንካራ ስብዕና የመፍጠር፣ የስራ ክፍፍልን የማስተማር፣ ታማኝነትን የማስተማር፣ ሳይንስና ቴክኖሎጅ እድገትና ሽግግር እንዲያመጣ የማድረግ፣ ግልጸኝነትን የማስተማር፣ መከባበርን የማስተማር እና ተጠያቂነትን የማስተማር ሚና ያላቸው መሆኑን የጥናት ውጤቱ አሳይቷል፡፡


**ቁልፍ ቃላት፡** ሀገረሰባዊ እምነት፣ የሃገረሰባዊ እምነት ሚና፣ የአማራ ማህበረሰብ፣ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ

[1] በዚህ ጥናት ውስጥ የቃላት ድግግሞሽን ለማስቀረት ሲባል፣ ‹‹ሚና›› ለሚለው ቃል ‹‹ፋይዳ››፣ ‹‹ጠቀሜታ›› እና ‹‹አበርክቶ›› የሚሉ ቃላት በተለዋጭነት ተክተው እንዲያገለግል ተደርጓል፡፡

**መግቢያ**

በፎክሎር አጥኝዎች ፎክሎር በተለያዩ ዘርፎች ተከፋፍሎ እንደሚጠና (Sims and Stephens, 2011; ፈቃደ፣ 1991 ዓ.ም[2]; Dorson, 1972) ይገልጻሉ፡፡ ተዘወትረው ከሚጠቀሱ ዋና ዋና ምድቦች መካከል ሀገረሰባዊ ልማድ አንዱ መሆኑን (Sims and Stephens, 2011; ሰሎሞን፣ 2007 ዓ.ም) ይጠቁማሉ፡፡ በሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ ደግሞ ሀገረሰባዊ እምነት እንደ አንድ ንዑስ ዘውግ በመሆን እንደሚጠና (Georges and Jones, 1995; Green, 1997; Sims and Stephens, 2011) ያስረዳሉ፡፡

ሀገረሰባዊ እምነት የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈጠረው በእንግሊዛዊው ፎክሎሪስት ላውሬንስ ጎሜ 1892 ነው (Tripura, 2025)፡፡ ሀገረሰባዊ እምነት በውስጡ አካቶ ከሚይዛቸው ጉዳዮች ብዙነት፣ ከሌሎች የፎክሎር ዘውጎች ጋር ባለው የጠበቀ ውስብስብ ትስስር ምክንያት፣ በጊዜ ሂደት ከሚያሳያቸው ለውጦች አንጻር፣ ከባህል ባህል በሚኖሩ ልዩነቶች፣ በዘርፉ ባለሙያዎች መካከል በተለያየ ምክንያት በሚኖር የአረዳድና ግንዛቤ መለያየት፣ ወዘተ ለሁሉም የሚመች አንድ ወጥ ማብራሪያ ማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡ ቢሆንም ግን በዚህ ጉዳይ ላይ የተለያየ ሀሳብ ከሰጡ ባለሙያዎች መካከል Green (1997) ተጠቃሽ ናቸው፡፡

Green (1997) ሀገረሰባዊ እምነት በተለያዩ ልማዳዊ አገላለጾች፣ ህዝባዊ እምነት፣ አስማት፣ ልዕለ ተፈጥሮ፣ የባልቴት ተረቶች፣ ሀገረሰባዊ መድሃኒት፣ ሀገረሰባዊ ሃይማኖት፣ የአየር ትንበያ እውቀት፣ የእጸዋት እውቀት፣ ጥንቆላ፣ ገደቢስነት፣ የስራ እውቀት፣ ትንበያዎች፣ ገጸምልክቶች፣ ክታቦችን እና የነውር አገላለጾችንና ባህርያትን አካትቶ የሚይዝ እንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡

ሀገረሰባዊ እምነት አንዱ የሀገረሰባዊ ልማድ ንዑስ ዘውግ ሲሆን፣ ወደ ፊት እንዲሆንልን ከምንፈልጋቸው ወይም ሊከሰትብን ከማንፈልጋቸው ውጤቶች በመነሳት ከተግባራዊ ምክሮች፣ ከድርጊቶችና ከጥንቃቄዎች፣ ከታድነነት ከመሳሰሉት የእለት ከዕለት ድርጊቶች አንስቶ ስለምናየው ተፈጥሯዊ ዓለም እንዲሁም ስለማይታዩት ምናባዊ ዓለማት ያለንን እይታ የማሳወቅ ሂደት ድረስ ያሉ መሰረታዊ ጽንስ ሀሳቦችን የሚይዝ የልማድ ዘርፍ እንደሆነ

---
[2](ዓ.ም) የሚል ያላቸው የቀን አቆጣጠሮች በኢትዮጵያ አቆጣጠር የተጻፉት ሲሆኑ ቀሪዎቹ ሁሉም የአውሮፓዊያንን የቀን አቆጣጠር የተከተሉ ናቸው፡፡

*የሚገልጹት ደግሞ ሰሎሞን* (2007 *ዓ.ም*)፤ Sims and Stephens (2011); *እና* Georges and Jones (1995) *ናቸው*።

*ሀገረሰባዊ እምነት ሲባል የሚታመኑ ነገሮች እና በማመን የሚተገበሩ ድርጊቶችን በአንድ ላይ የሚጠቁም ቃል እንደሆነ የሚያመለክቱት ደግሞ* ÓConnor (1995) *ናቸው። ለዚህም ነው ሰሎሞን* (2007 *ዓ.ም*) ‹‹…*ሀገረሰባዊ እምነት ስንል ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮችን ይይዛል ማለት ነው። እነሱም አማኙ፣ የሚታመነው ነገር እንዲሁም በአማኙና በሚታመነው ነገር መካከል ያለው የማመን ሂደት ናቸው*›› *ሲሉ የሚገልጹት*።

*ከላይ ከተነሳው ዝርዝር የባለሙያ ሀሳብ መሰረት ሀገረሰባዊ እምነት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በትውልድ ቅብብሎሽ የሚገኝ አካባቢያዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ መሰረትን መነሻ አድርጎ ሊዳብር የሚችል ማህበረሰቡ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ብሎ የሚያውቃቸውና የሚያምንባቸው አገላለጾችን፣ ዝንባሌዎችን፣ ሀገረሰባዊ እውቀቶችን፣ አስተሳሰባዊ ፍልስፍናዎችን፣ ቁሳዊ ውክልናዎችን፣ እምነታዊ ክዋኔዎችን የሚያመለክት ነው ሊባል ይችላል*።

*የዚህ ጥናት ዋና ትኩረትም ከሀገረሰባዊ ልማድ ንዑስ ዘርፎች ውስጥ አንዱ የሆነው ሀገረሰባዊ እምነት ነው። ጥናቱ የተካሄደው በአማራ ክልል በሚገኘው የደጀን ወረዳ ማህበረሰብ ሲሆን፣ ዓብይ ዓላማውም በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኑ ሀገረሰባዊ እምነቶችን ሚና መመርመርና ተገቢ ትንተና ማድረግ ነው። በጥቅሉ ከሀገረሰባዊ እምነት ጋር በተየያዘ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ እስከ አሁን የተሰሩ ጥናቶች (ለምሳሌ፡- ፀዳለ*፣ 2007 *ዓ.ም*፤ *በኃይሉ*፣ 1953 *ዓ.ም*፤ *ሞላ*፣ 2009 *ዓ.ም*፤ *ሙሉቀን*፣ 2001 *ዓ.ም*፤ *ዋልተንጉስ*፣ 2007 *ዓ.ም*፤ *መኮንን*፣ 1982 *ዓ.ም*፤ *ዩፍታሄ*፣ 1953 *ዓ.ም*፤ *አይናዲስ*፣ 2013 *ዓ.ም*፤ *ፍስሃ*፣ 1953 *ዓ.ም*፤ *ኮማንደር*፣ 2005 *ዓ.ም*፤ *ግርማ*፣ 2003 *ዓ.ም*፤ *ማሞ*፣ 2002 *ዓ.ም*፤ *ነጻነት*፣ 1996 *ዓ.ም*፤ *መኮንን*፣ 1973 *ዓ.ም*) *ቢኖሩም አንዳቸውም ግን የሀገረሰባዊ እምነቶችን ሚና የመረመሩና ተገቢ ትንተና የሰጡ ሆነው አልተገኙም። ብዙዎቹ አጥኝዎች (ለምሳሌ፡- ኮማንደር*፣ 2005 *ዓ.ም*፤ *ግርማ*፣ 2003 *ዓ.ም*፤ *ማሞ*፣ 2002 *ዓ.ም*፤ *ነጻነት*፣ 1996 *ዓ.ም*፤ *እና መኮንን*፣ 1982 *ዓ.ም*) *እንደ ቅደም ተከተላቸው የሀገረሰባዊ እምነቶቹን ስረዓተ ከበራ፣ እምነታዊ ድርጊቶችን፣ የሀገረሰባዊ እምነቶች ቃል ግጥሞች ከመተንተን ባለፈ አዎንታዊ ፋይዳውን ለማሳየት አልሞከሩም። ይህም ለዚህ ጥናት ዋና መነሻ ምክንያት ሆኗል*።

## የጥናት ቦታ

ደጀን ወረዳ በአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም ዞን የሚገኝ ሲሆን፣ ከአዲስ አበባ 229 ኪ.ሜ፣ ከባህር ዳር 335 ኪ.ሜ እና ከደብረ ማርቆስ 70 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ በምስራቅ ከሸበል በረንታ፣ በሰሜን ከእነማይና ደባይ ጥላት ግን፣ በምዕራብ ከአዋበል እና በደቡብ ከኦሮሚያ ክልል ወረ ጃርሶ ጋር ይዋሰናል፡፡ ወረዳው 22 የገጠር እና 2 የከተማ ቀበሌዎች አሉት፡፡

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 2022 የህዝብ ቆጠራ መሠረት፣ 97.01% የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ተከታዮች፣ 2.85% የእስልምና እና 0.14% ያህሉ ደግሞ የሌሎች ሃይማኖቶችና እምነቶች እንደሆኑ ከወረዳው ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ከ131,930 አጠቃላይ ህዝብ ውስጥ 8.28% የከተማ ነዋሪዎች ሲሆኑ፣ 91.72% በገጠር አካባቢ የሚኖር መሆኑን ነው ከተገኘው መረጃ ማወቅ የተቻለው፡፡ የማህበረሰቡ ቋንቋ አማርኛ ሲሆን የዕለት ተዕለት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች በዚሁ ቋንቋ ይከናወናሉ፡፡

**የአጠናን ስነ-ዘዴ**

ይህ ጥናት በደጀን ወረዳ አማራ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ሀገረሰባዊ እምነቶችን ሚና የሚመረምርና ተገቢ ትንተና የሚያደርግ በመሆኑ አይነታዊ የምርምር ንድፍን የተከተለ ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚው በደጀን ወረዳ ለረጅም ጊዜ በመስክ በመቆየት የጥናት መረጃዎችን ሰብስቧል፡፡ በወረዳው ከሚገኙ 24 ቀበሌዎች ውስጥ የተሰበሰቡ መረጃዎች ወረዳውን ከአኗኗር ዘይቤ እና ከአየር ንብረት አንጻር ይወክላሉ (ያሳያሉ) ተብለው የታመነባቸው ሰባት ቀበሌዎች ማለትም ኩራር፣ ምንጅ፣ ገልገሌ (በቆላማውና በገጠር አካባቢ የሚኖረውን የማህበረሰብ ክፍል ወካይ)፣ አቃቤት፣ ቆንቸር (በገጠርና ወይና ደጋ የአየር ጠባይ ያለው)፣ ደጀን ከተማ 01 ቀበሌ (ሙሉ በሙሉ የከተማ ነዋሪዎች የሆኑና ወይና አደጋ የሆነ) እና የትኖር (በከፊል ከተማ ቀሪው በገጠር የሚኖር፣ ደጋማ የአየር ንብረት ያለው) በአላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ የመረጃ መሰብሰቢያ ቦታዎች ተደርገዋል፡፡ ምክንያቱም ይህ የናሙና አመራረጥ ዘዴ፣ አጥኚው የጥናቱን ቦታዎች የሚመርጠው ከጥናቱ ዓላማ አንጻር ስለሆነ የትኞችን ቦታዎች ብመርጥ ይሻላል? የትኞቹ የጥናቱ አካላይ ቦታዎች በጥናቱ ቢካተቱ የተሟላና ትክክለኛ መረጃ ላገኝባቸው እችላለሁ? የሚሉ ጉዳዩችን መነሻ በማድረግ ቦታዎችን ወይም ሌሎች ነገሮችን መምረጥ እንደሚገባው (Given, 2008) ይመክራሉ፡፡

ሌላው መሰረታዊ ነገር የሚመረጡ መረጃ ሰጪዎች ከብዙ ጉዳይና መመዘኛ አንጻር ከወረዳው የሚሰበሰበውን መረጃ ሊወክሉ የሚችሉ ሆነው የተመረጡ መሆን እንዳለበት Sapsford and Jupp (2006) የተባሉ የዘርፉ ባለሙያ ይጠቁማሉ፡፡

ስለሆነም ለዚህ ጥናት ለናሙናነት የተመረጡ መረጃ አቀባዩች የወረዳውን ማህበረሰብ ከእድሜ፣ ከ35-75 ባለው የእድሜ ክልል የሚገኙ፣ ከአየር ንብረት፡- ቆላ፣ ወይና ደጋና ደጋ ነዋሪዎች፣ ከአኗኗር ዘይቤ አንጻር በከተማና በገጠር የሚኖሩ፣ ሁለቱም ጾታዎች፣ ከሙያ አንጻ፡- አርሶ አደር፣ ነጋዴ፣ የመንግስት ሰራተኛ፣ አርብቶ አደር፣ ማህበራዊ ደረጃ፡- የሀገር ሽማግሌዎች፣ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች፣ የትምህርት ደረጃ፡- ማንበብና መጻፍ ከማይችሉ አንስቶ የመጀመሪያ ዲግሪ እስካላቸው ሰዎች እና የጠለቀ የቤተ-ክህነት ትምህርት እስከተማሩ ሰዎች ድረስ ያሉ የተጠኘው ማህበረሰብ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተከታይ አባላት በመረጃ ሰጭነት ተሳትፈዋል፡፡ በእነዚህ የሃይማኖት ተከታዮች ላይ ብቻ የመወሰኑ ምክንያት ደግሞ የመረጃ መጠን እና የጊዜ ከልክ እንዳያልፍ በማሰብ፣ የገንዘብ ሁኔታ ከግምት በማስገባት እና የተሰበሰበውም መረጃ ለማሟያ ጥናቱ በቂ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

እነዚህ ነገሮችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ለናሙናነት ከተመረጡ ሰባቱ ቀበሌዎች በቅርብ ሰዎች ጥቆማ ወይም በቅብብሎሽ አስረጅ የናሙና አመራረጥ እና ኢላማዊ የናሙና አመራረጥ ዘዴዎችን እንደአስፈላጊነቱ በመጠቀም ከእያንዳንዱ ሶስት ሶስት በአጠቃላይ 21 ቁልፍ መረጃ አቀባዮችና ከቆንቸርና አቃቤት ቀበሌዎች ከእያንዳንዳቸው አምስት አምስት፣ ኩራር፣ ገልገሌና ምንጅ ቀበሌዎች ከእያንዳንዳቸው አራት አራት፣ ከየትኖራና ከደጀን 01 ቀበሌዎች ደግሞ ከእያንዳንዳቸው ሶስት ሶስት በአጠቃላይ 28 አጋዥ መረጃ አቀባዮች ሲኖሩ፣ በድምሩ 49 መረጃ አቀባዮች ተሳትፈዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ 11 ሴቶች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ደግሞ ወንዶች ናቸው፡፡

የፎክሎር ጥናት በአመዛኙ የመስክ ስራ ስለሆነ ብዙን ጊዜ የሚጠቀማቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት ናቸው (Sims and Stephens, 2011)፡፡ ይህ ጥናትም የመስክ ጥናት እንደመሆኑ መጠን አጥኚው በቀዳማይ የመረጃ ስልትነት የሚያገለግሉትን ምልከታ (ተሳትፏዊና ኢ-ተሳትፏዊ)፣ ቃለ መጠይቅ (ኢ-መደበኛና መደበኛ) እና ቡድን ተኮር ውይይት በዋናነት ጥቅም ላይ በማዋል የጥናቱን መረጃዎች ሰብስቧል፡፡

ሌላው አንድ ኢትኖግራፈር (የመስክ አጥኝ) ትክክለኛና የተሟላ መረጃ መሰብሰብ እንዲችል ከተጠኘው ማህበረሰብ ጋር ለረጅም ጊዜ አብሮ መቆየት እንዳለበት (Murchison, 2010;

Fetterman, 2010; ፈቃደ፣ 1991 ዓ.ም) ይጠቁማሉ፡፡ በዚህ ጥናትም የሚሰበሰቡ መረጃዎችን ብቃትና ታማኝነት ከፍ ለማድረግና የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ይረዳ ዘንድ አጥኚው በሁለት የተለያዩ ዙሮች (ዙር አንድ ከግንቦት 01/ 2016 ዓ.ም እስከ ነሃሴ 30/ 2016 ዓ.ም ድርስ የተደረገ ሲሆን፣ ሁለተኛው ዙር ደግሞ ከመስከረም 01/ 2017 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30/ 2017 ድረስ) የመስክ የመረጃ ስብሰባ ስራዎችን አድርጓል፡፡

የፎክሎር ጥናቶች እንደአስፈላጊነቱ ሊጠቀሟቸው የሚችሉ ተፈጥሯዊ፣ አርቴፊሻል እና ቅንብር ተፈጥራዊ አውዶች (መቼቶች) እንዳሉ Goldstein (1964) እና ፈቃደ (1991 ዓ.ም) ይገልጻሉ፡፡ በዚህም መሰረት አጥኚው ተፈጥሯዊና አርቴፊሻል መቼቶችን በመጠቀም የጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችሏል፡፡ በመጨረሻም የተሰበሰቡ መረጃዎችን ገላጫዊ በሆነ ስልት የመረጃ ትንተናና ትርጎማ ለማድረግ ሞክሯል፡፡

**ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ**

**ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ (Functional Theory)**

ይህ ንድፈ ሀሳብ ሲነሳ ስማቸው በቀዳሚነት ከሚጠቀሱት ምሁራን ውስጥ ፈረንሳያዊው ፈላስፋና ሶስዮሎጅስት የነበሩት Email Durkheim አንዱ ናቸው (Turner and Maryanski, 1979)፡፡ እንደ እሳቸው ገለጻ በማህበረሰቡ ውስጥ ከትውልድ ወደ ትውልድ በቅብብሎሽ የመጡና የማህበረሰቡ አባላት የሚያውቋቸውና የሚጋራቸው ባህላዊ እሴቶች፣ ስነ-ምግባሮች፣ መሰረታዊ ልማዶች፣ ማህበራዊ እምነቶችና የግብረገብ ህጎች አሏቸው፡፡ እነዚህ ማህበራዊ ክስተቶች ደግሞ የማህበረሰቡን ሁለንተናዊ አንድነትና ትስስር ትርጉም ያለው ከማድረግ አኳያ የራሳቸው ፋይዳ እንዳላቸው (Barnard, 2004; Green, 1997) ይገልጻሉ፡፡

እንደ Malinowski, (1944) ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ እይታ ደግሞ የሰው ልጅ ሰባት መሰረታዊ ፍላጎቶች እንዳሉት ይጠቅሳሉ፡፡ እነሱም፡-ምግብ፣ ዘር መተካት፣ አካላዊ ምቾት፣ ደህንነት፣ መዝናናት፣ እንቅስቃሴና እድገት ናቸው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ማህበራዊ መዋቅርና በዚያ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ባህላዊ እሴቶች ለእነዚህ መሰረታዊ የሰው ልጅ ፍላጎቶች መሟላትና ምላሽ ማግኘት እንዲያገለግሉ ሆነው የተፈጠሩ ናቸው ይላሉ፡፡ ምክንያቱም የባህል አካል የሆነ ማንኛውም ነገር (የፎክሎር ቅንጣት) የራሱ የሆነ ሚና አለው (Barnard, 2004; Green, 1997) ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

ከዚህ ጋር በተየያዘ በፎክሎር ጥናት ውስጥ የተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ትኩረት ማህበረሰብ ወይም ፎክ ቡድን አባላት በሚጋሯቸው እሴቶች እንዴት እንደሚግባቡ ላይ እንደሚመሠረት በ Bascom (1954) እና Sims and Stephens (2011) ተገልጿል። በእነዚህ እሴቶች ውስጥ ሀገረሰባዊ እምነቶች የጥናቱ ዋና ትኩረት ናቸው። እንደ Radcliffe-Brown (1952) ገለጻ ሀገረሰባዊ እምነቶችን እንደ ማህበራዊ መዋቅር አካል በመመልከት ለማህበረሰቡ አንድነት እና ስርዓት መጠበቅ እንደሚረዱ ይገልጻሉ። አክለውም ሀገረሰባዊ እምነቶች ማህበራዊ ደንቦችን ለማጠናከር እና የቡድን መለያየትን ለመጠበቅ ጠቀሜታ እንዳላቸው አመልክተዋል።

Durkheim (1915) እንደሚገልጹት ሀገረሰባዊ እምነቶች ሰዎችን በተጋራ እምነትና እሴት በማስተሳሰር ማህበራዊ አንድነትን ያጠናክራሉ። በተጨማሪም ባህላዊ እሴቶችንና ልምዶችን ከትውልድ ወደ ትውልድ በማስተላለፍ የባህል ቀጣይነትን ያረጋግጣሉ። እንዲሁም Ben-Amos (1971) ሀገረሰባዊ እምነቶች በማህበራዊ አውድ ውስጥ የሚፈጠሩና የሚተገበሩ መሆናቸውን ያብራራሉ። እንደ እርሳቸው ገለጻ እነዚህ ባህላዊ ዕውቀቶች ለማህበራዊ መግባባት እና ለባህላዊ ቀጣይነት ትልቅ ሚና ይጫወታሉ።

በ Malinowski (1948) መሠረት ሀገረሰባዊ እምነቶች ባህላዊ እሴቶችን ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ ለማስተላለፍ ዋና መንገድ ይሆናሉ። በዚህ መሠረት ሀገረሰባዊ እምነቶች የህዝብ ልማዳዊ ልምዶችን፣ እሴቶችን፣ እና አመለካከቶችን በማስቀጠል የባህል ቀጣይነትን ያረጋግጣሉ። እንዲሁም እነዚህ እምነቶች ሰዎች በሕይወታቸው ሊያጋጥማቸው የሚችሉ የፍርሃት፣ የጭንቀት ወይም ያልታወቁ ሁኔታዎችን ለመቀነስ እንደ ስነ-ልቡና ድጋፍ ያገለግላሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ Dundes (1980) ሀገረሰባዊ እምነቶች በማህበረሰብ ውስጥ ስነ-ልቡናዊና ማህበራዊ ተግባራት እንዳላቸው ያመለክታሉ። እነዚህ እምነቶች የሰዎችን ፍርሃት፣ ተስፋ እና ማህበራዊ እሴቶች ለመግለጽ እንደሚረዱ ይገልጻሉ፤ እንዲሁም የቡድን መለያየትን እና ባህላዊ ማንነትን ለመጠበቅ ወሳኝ ሚና እንዳላቸው ያብራራሉ።

እንደ Bascom (1954) ደግሞ ሀገረሰባዊ እምነቶች በተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ አቅጣጫ የማስተማር፣ የማዝናናት፣ ለባህላዊ እሴቶች እውቅና የመስጠት እና ማህበራዊ ልምዶችን የመጠበቅ ተግባራት እንዷሏቸው ይገልጻሉ። በዚህ አንፃር ሲታይ ሀገረሰባዊ እምነቶችም የማህበረሰቡን እሴቶች ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ እና የተለመዱ ባህላዊ ልምዶችን ለማስጠበቅ አዎንታዊ ሚና እንዳላቸው ይጠቁማሉ።

በመጨረሻም የተወሰኑ ሀገረሰባዊ እምነቶች ደግሞ ማህበረሰቡን ከበሽታ አስቀድሞ በመከላከል ወይም በመፈወስ ጤናማ እንዲሆን፣ በስራ በውትድርና፣ በምርታማነት፣ ወዘተ ስኬታማ እንዲሆን የሚያግዙ ናቸው (Kabak, 2025)፡፡ በአጠቃላይ ሀገረሰባዊ እምነቶች ማህበረሰብን ለመጠበቅ፣ ለመደገፍ እና ለማስቀጠል በርካታ ተግባራት ያላቸው መሆናቸው ይገልጻል፡፡

የዚህ ጥናት ዓላማ ደግሞ ቀደም ሲልም እንደተጠቀሰው የተጠኘውን ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ እምነቶች ሚና መመርመርና ተገቢ ትንተና ማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም ከዚህ ንድፈ ሀሳብ እይታ አንጻር ከመስክ የተሰበሰቡ የጥናት መረጃዎች በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ ያላቸው ፋይዳ ምን ይመስላል? የሚለውን ለመመርመርና ለመተንተን ሲባል ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

## የጥናቱ ትንተና እና ግኝቶች

ሀገረሰባዊ እምነት ከጥንት ጀምሮ እስከ አሁን ድርስ ያሉ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን አካቶ የሚይዝ ነው (Kabak, 2025)፡፡ ሀገረሰባዊ እምነት ምንም እንኳን ከአካባቢ፣ ከባህል፣ ከቋንቋ፣ ከሃይማኖት፣ ወዘተ መለያየት ጋር ተያይዞ ሊለያይ የሚችልበት ሁኔታ ያለ ቢሆንም ነገር ግን በማንኛውም የዕድገት ደረጃ ላይ በሚገኝ የማህበረሰብ ክፍል ውስጥ የማይታጣ ሰብአዊ እሴት ነው (Harmankaya and Atagence, 2022)፡፡ ምክንያቱም በአንድ ማህበረሰብ ወይም ህዝብ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነ-ምህዳራዊ፣ እና በሌሎች ጉዳዮች ላይ የራሱን ጥቅም ከማስገኘት በዘለለ በዕለት ከዕለት ህይወታቸው ማለትም በአመጋገብ ስረዓት፣ በአለባበስ፣ በቤት አሰራር፣ በጋብቻ በለቅሶና በጋብቻ ስረዓተ ከበራዎች፣ ወዘተ ውስጥ ወሳኝ ሚና ይጫዎታል (Liu, 2023)፡፡ የባህል አካል የሆነ ማንኛውም ነገር (የፎክሎር ቅንጣት) የራሱ የሆነ ሚና አለው (Barnard, 2004; Green, 1997) መባሉም ለዚህ ነው፡፡

ስለሆነም በዚህ የጥናቱ ክፍል ውስጥ በምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና ቡድን ተኮር ውይይት ያሉ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በመጠቀም ከመስክ በተሰበሰቡ መረጃዎች የትንተና ውጤት መሠረት፣ ሀገረሰባዊ እምነቶች በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ ያላቸውን ሚና ለማቅረብ ጥረት ተደርጓል፡፡

ሆኖም ግን ከተገኘው የመረጃ ትንተናና የጥናት ውጤት ባሻገር አንድ ሀገረሰባዊ እምነት በባህርይው አንድና ከዚያ በላይ የሆነ ጠቀሜታ ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ የተነሳ የአንደኛው ሀገረሰባዊ እምነት ፋይዳ በሌላኛው ውስጥ የሚገኝበት ሁኔታ ይታያል፡፡

ይህን የሚና መዛነቅ መልክ ለማስያዝና የሃሳብ ድግግሞሽን ለማስቀረት ሲባል ደግሞ የአንድን ሀገረሰባዊ እምነት እያንዳንዱን ዝርዝር ጉዳይ ለማሳየት ከመሞከር ይልቅ አንደኛው ከሌላኛው ጎልቶ ከሚታይ አንድ ሚናው አንጻር ብቻ በመዳሰስ ሊኖረው የሚችለውን አበርክቶ ለማሳየት ጥረት ተደርጓል፡፡

በዚህ መሰረት የተጠኘው ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ እምነቶች በዋናነት ጤናማ ማህበረሰብ የመፍጠር፣ ሃይማኖታዊ ዶግማን የማስከበርና የማስቀጠል፣ አካባቢያዊ ስነ-ምህዳርን የማስጠበቅ፣ መልካም ስብዕናን የማስተማር፣ ስነ-ልቡናዊ እረፍት የመፍጠር፣ የሰብአዊነት ባህርይን የማጎልበት፣ ኢኮኖሚን የማሳደግ፣ ማህበራዊ አንድነትና ትስስር እንዲጠነክር የማድረግ፣ ባህልን የማጽናትና የማስቀጠል፣ ጠንካራ ስብዕና የመፍጠር፣ የስራ ክፍፍልን የማስተማር፣ ታማኝነትን የማስተማር፣ ሳይንስና ቴክኖሎጅ እድገትና ሽግግር እንዲያመጣ የማድረግ፣ ግልጸኝነትን የማስተማር፣ መከባበርን የማስተማር እና ተጠያቂነትን የማስተማር ፋይዳ ያላቸው መሆኑን ነው ማረጋገጥ የተቻለው፡፡ በዚሁ መሰረትም ከመስክ የተሰበሰቡና ትንተና የተደረገባቸውን ሁሉንም ሀገረሰባዊ እምነቶች በዚህ ጥናት ውስጥ ማንሳት ተገቢም አስፈላጊም ነው ተብሎ አልታሰበም፡፡ ሆኖም ግን የሁሉንም ሀገረሰባዊ እምነቶች ፋይዳ ወካይ ሊሆኑ የሚችሉ የተወሰኑትን ሀገረሰባዊ እምነቶች በማሳያነት በማምጣት እንደሚከተለው በትንታኔ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

1. **ጤናማ ማህበረሰብ የመፍጠር ሚና**

የተጠኘው ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ እምነቶች ከሚሰጧቸው በርካታ ተግባራዊ ፋይዳዎች ውስጥ አንዱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ማህበረሰቡ ጤናማ እንዲሆን የማገዝ ተግባር ያላቸው ናቸው ሊባል ይችላል፡፡

**አስረጅ፡- የተስተካከለ አለባበስ (አጊያጊያጥ) የሚፈለግ መሆኑ**

በደጀን ወረዳ ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ እምነት ለወንድም ሆነ ለሴት ተገቢ ነው ተብሎ የሚታሰብና ተለይቶ የሚታወቅ የአለባበስ እና አጊያጊያጥ አካባቢያዊ ያልተጻፈ ህግ አለ፡፡ በዘርፉ ባለሙያዎች ‹‹Clothing traditions as well as folk beliefs are an important part of culture in communities›› (Harmankaya and Atagence, 2022) እንደሚባለው ማለት ነው፡፡

በዚህ ምክንያት፡- ሴቶች ከመጠን ባለፈ መልኩ ደረትን፣ ጀርባን፣ ጡትን፣ እምብርትን፣ ዳሌን፣ ወዘተ የሚያሳይ አለባበስ፤ የተገላለጠ ባይሆንም ነገር ግን ከልክ ባለፈ መልኩ ከሰውነት ጋር

ከመጣበቁ የተነሳ የጡትን፣ የመቀመጫን፣ የፓንትን፣ የመራቢያ አካላትን፣ ወዘተ ቅርጽ ሊያሳይና ሊያስገምት የሚችል አለባበስ፤ የቤት ውስጥም ሆነ የውጭ ስራን በተለመደው መንገድ በምቾት ለማከናወን ሊያስተጓጉል ወይም ሊከለክል የሚችል አለባበስ፣ ተቀባይነት የለውም፡፡ አጊያጊያጥን በተመለከተ ደግሞ ሴት ልጅ መጠኑ ትልቅ የሆነ የጆሮ ጌጥ፣ መነጸር፣ ሂል ጫማ፣ የእጅ አምባር፣ የአንገት ሃብል፣ ኮፍያ ወይም ባርኔታ፣ ወዘተ መጠቀምና ማድረግ ተቀባይነት የሌላቸው ተግባራት መሆናቸውን ነው ማረጋገጥ የተቻለው፡፡

የወንዶች አለባበስ (አጊያጊያጥ) በተመለከተ ደግሞ፡-ከዚህ በፊት በአካባቢው ከሚታወቀው ውጭ ባልተለመደ አኳኋን የሴቶችን፣ ወይም የብዙሃኑን ሰው ትኩረት ሊስብ በሚችል ሁኔታ መልበስና ማጌጥ (ከልክ ያለፈ ሰፊ ወይም ጠባብ ሱሪ፣ ሸሚዝ፣ ቲሸርት፣ ወዘተ መልበስ እና ከመጠን በላይ ወፍራም ወይም ረጅም የሆነ ከተለያየ ነገር የተሰራ የአንገትና የእጅ ዘለበት ማድረግ፣ እንግዳ የሆነ መጠንና ቀለም ያለው መነጸር፣ ቆብ፣ ባርኔታ ማድረግ፣ ፀጉርን ማሳደግ፣ ወዘተ)፣ ያልተፈለገ የሰውነት ክፍልን (ጉልበትን፣ ባትን፣ መቀመጫን፣ ደረትን፣ ወዘተ) በከፊል ወይም በሙሉ ሊያሳይ የሚችል አለባበስ፣ ለስራ የማይመች አለባበስ፣ ወዘተ ከአንድ ጨዋና ስረዓት አለው ተብሎ ከሚታሰብ ሰው የማይጠበቁ ተግባራት ናቸው (አቶ ፋሲካው ደጀን፣ ቃለ መጠይቅ፣ 09/ 03/ 2017 ዓ.ም፣ ገልገሌ)፡፡

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩ የሴትም ሆነ የወንድ አለባበሶችና አጊያጊያጦችን ማድረግ በማህበረሰቡ አስተሳሰብ ከሚያሰጠው አሉታዊ ባህሪያዊ ውክልና ባሻገር በተጠቃሚው የማህበረሰቡ አባል ላይ ሊያመጡ የሚችሉት አደጋና የጤና ችግር ቀላል እንዳልሆነ በተለያዩ የሚዲያ አማራጮች የሚቀርቡ የባለሙያ ምክርና ማስጠንቀቂያዎች ምስክር ናቸው፡፡

ለምሳሌ ያህል፡- አካላዊ መራቆት የሚታይበት አለባበስ ለምች፣ ለቆዳ ካንሰር፣ ለብርድ፣ ለፀሃይ እንዲጋለጡ ማድረግ፤ ከሰውነት ጋር የተጣበቀ አለባበስ ደግሞ ለኩላሊት፣ ለቆዳ አለርጅ እና ተየያዥ በሽታዎች እንደሚያጋልጥ፤ ሂል ጫማ መጠቀም ደግሞ ለማህፀን ኢንፌክሽን፣ ለኩላሊት ህመም፣ ለዳሌ ህመምና መሰል ተየያዥ በሽታዎች እንዲጋለጡ እንደሚያደርግ ይናገራሉ፡፡ ከዚህ አንጻር የእነዚህና መሰል ተዛማጅ ሀገረሰባዊ እምነቶች መከበርና መጠበቅ መቻል የተጠኘውን ማህበረሰብ አባላት ጤናማና አምራች ዜጎች እንዲሆኑ ከማስቻል አንጻር ሊኖራቸው የሚችለው ሚና ቀላል እንደማይሆን መናገር ይቻላል፡፡ ለዚህም ይመስላል Kabak (2025) ሀገረሰባዊ እምነቶች አንድን ህዝብ ወይም ማህበረሰብ…እንዲሁም የማህበረሰቡ አባላት ለጥቃትና ጉዳት እንዳይጋለጡ የማድረግ ሚና አላቸው ሲሉ የሚገልጹት፡፡

## 2. ሃይማኖታዊ ዶግማን የማስከበርና የማስቀጠል ሚና

የተወሰኑት ሀገረሰባዊ እምነቶች ደግሞ የጥናቱ ዋና ትኩረት የሆነውና ከአካባቢው ነዋሪ ከፍተኛ ቁጥር የሚይዘውን የማህበረሰብ ክፍል እየተከተለ ያለውን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ሃይማኖት ዶግማና ቀኖናዎች እንዳይጣሱ፣ እንዲከበሩና ቀጣይነት እንዲኖራቸው የማድረግ ፋይዳ ያላቸው ሆነው ይታያሉ፡፡ አንዳንድ ሀገረሰባዊ እምነቶች የተቀደሱ ከሚባሉ ነገሮች ጋር ትስስር እንዲኖረን የማድርግ ተግባር ያከናውናሉ (Kabak, 2025)፡፡

**አስረጅ፡-ለእርድ የሚቀርቡ እንስሳት ሸሆና (ሸኮና) ክፍትና ልምዣክ የሚገለብጡ መሆን እንዳለባቸው**

የደጀን ወረዳ ማህበረሰብ ከግብርናና ንግድ በተጨማሪ የተለያዩ የቤት እንስሳትን በማርባት ኑሮውን ይገፋል፡፡ ለምሳሌ፡-በቆላማውና በወይና ደጋው አካባቢ የሚገኘው የማህበረሰብ ክፍል በብዛት ፍየል፣ አህያ፣ በሬ፣ ላም፣ ዶሮ፣ ድመት፣ ውሻ ያረባል፡፡ በደጋው የአየር ንብረት የሚገኙት ደግሞ ከላይ ከተጠቀሱት እንስሳት በተጨማሪ ፈረስና በቅሎ በብዛት ያረባል፡፡ እነዚህን እንሰሳትም ለተለያየ ዓላማና ተግባር ይጠቀማችዋል፡፡ ከዚህ ውስጥ አንዱ ለምግብነት ማዋል ነው፡፡

ሆኖም ግን ማህበረሰቡ እነዚህን ሁሉ እንስሳት ለእርድ አይፈቅድም፡፡ ለዚህም የራሱን ትክክል ነው ብሎ የሚያምንበትን ማህበረሰባዊ ምክንያት ያቀርባል፡፡ ከሚያቀርባቸው ምክንያቶች ውስጥ ሸሆና (ሸኮና) ክፍት መሆንና ልምዣክ መገልበጥ መቻል ዋነኞቹ ናቸው፡፡ ምክንያቱም በተጠኚው ማህበረሰብ እምነት ሸሆና ክፍትና ልምዣክ የሚገለብጡ እንስሳት በእግዚያብሄር የተባረኩ፣ ስጋቸውም ቅዱስ ነው፣ ሲበሉትም ጤና ነው ብለው የሚያምኑ ሲሆን፣ በአንጻሩ ከዚህ ውጭ የሆኑት እንሰሳት ደግሞ በእግዚያብሄር ያልተባረኩ በመሆናቸው ስጋቸው እርኩስ ነው፡፡ ስለሆነም ቢበሉት ያረክሳል፤ ለጤናም አይመች ተብሎ የሚታመን መሆኑን ይናገራሉ (የአጥኚው ምልከታ እና አቶ መረሻ ስዩም፣ ቃለ መጠይቅ፣02/ 10/ 2016 ዓ.ም፣ የትኖራ)፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በተጠኚው ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ እምነት የእነዚህ እንስሳት ለእርድ የሚፈቀዱ ወይም የማይፈቀዱ መሆን፣ ትክክል ወይም ስህተት መሆን፣ ስናይ ወይም እኩይ መሆን፣ ወዘተ ተብሎ የመለየት የከየት መጣ መስፈርት መሰረታዊ ፅንስ ሀሳባቸው ሲፈተሽ በዋናነት መነሻ ያደረጉት የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ዶግማና ቀኖና ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

ለምሳሌ፡-‹‹በብሉይ ኪዳን…፡፡ የኦሪትም መስዋዕቶች ከስጋ፣ ከእህልና ከመጠጥ ነበሩ፡፡ ከስጋም ሲሆን ነውር ከሌለባቸው ንጹሃን ከተባሉ እንስሳትና ወፎች መሆን ነበረበት፤ ዘፍ[3]. 8፣20፤ዘሌ[4]22፣17-25››፤የሚል መጽሃፍ ቅዱሳዊ ታሪክ እናገኛለን፡፡ በዚህ አገላለጽ መሰረት እንስሳትና አዕዋፋት በተፈጥሯቸው ንጹህ የሆኑና ነውር ያለባቸው ተብለው የተለዩ መሆኑን፣ እርድ ሲደረግም ይህንን ነገር ታሳቢ ማድረግ የሚገባ መሆኑን ፍንጭ የሚሰጥ መጽሃፍ ቅዱሳዊ ሓይል ቃል ነው፡፡ ስለሆነም በተጠኘው ማህበረሰብ የተለያየ የህይወት ገጽታ ውስጥ የዚህ ሀገረሰባዊ እምነት መጠበቅና መከበር መቻል በተዘዋዋሪ ለኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ዶግማና ቀኖና መከበርና ቀጣይነት የራሱ የሆነ ድርሻ ይኖረዋል ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህም ነው Durkheim (1915) በተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ እይታ ሀገረሰባዊ እምነቶች ሰዎችን በአንድ የተጋራ እምነት እና ልማዳዊ እሴት በማስተሳሰር የማህበረሰቡን መተባበር ያጠናክራሉ ሲሉ የሚገልጹት፡፡

## 3. አካባቢያዊ ስነ-ምህዳርን የማስጠበቅ ሚና

አንዳንድ የተጠኘው ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ እምነቶች ደግሞ የተጠኘው አካባቢ ተፈጥሯዊ ስነ-ምህዳሩ የተጠበቀ እንዲሆን ከማድረግ አኳያ የራሳቸው እግዛ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ሀገረሰባዊ እምነቶች ለተጠቃሚው ማህበረሰብ ከሚሰጡት አበይት ተግባራት ውስጥ አንዱ የመግታት ወይም የመቆጣጠር ተግባር ነው (Bascom, 1954)፡፡ ከዚህ ጋር በተየያዘ፡-

**አስረጅ፡-ዋንዛና አንቃ ዛፎችን እቤት በር ላይ መትከል የሚገባ መሆኑ**

ዋንዛ፡-ፍሬው የሚበላ፣ እንጨቱ ጠንካራ፣ ቅጠሉ ሰፋፊ የሆነ ትልቅ ዛፍ (የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣ 1993 ዓ.ም) ሲሆን፤ አንቃ (አንቋ)፡- ደግሞ በቆላና በወይና ደጋ የሚበቅል፣ እንጨቱ ኮርቻ ለመስራት ወይም በዋና ጊዜ ጀርባ ላይ ታዝሎ ለመንሳፈፍ የሚያስችል፣ እንደ አስቴ ሲሰበቅ እሳት ሊወጣው የሚችልና ቀላልነት ያለው የእፀዋት አይነት እንደሆነ (የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣ 1993 ዓ.ም) ይገልጻል፡፡ በተጠኘው አካባቢ የአንቃ ፍሬም ለምግብነት እንደሚውል በመረጃ ስብሰባ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

---

[3] ኦሪት ዘፍጥረት

[4] ኦሪት ዘሌዋውያን

በአካባቢው ማህበረሰብ እምነት እነዚህ ሁለት የእጸዋት አይነቶች በእርኩስ መናፍስት የማይወደዱና እርኩስ መናፍስቱን ከርቀት የማባረር ተፈጥሯዊ ኃይል አላቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለሆነም በበቀሉበት አካባቢ ድርሽ አይልም በሚል ይታሰባል፡፡

በዚህ ምክንያት በተጠኘው ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ እምነት በእያንዳንዱ ግለሰብ የመግቢያ በር ቀኝ በኩል እነዚህ የእጸዋት አይነቶች ቢተከሉ እንደሚመከር የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በአብዛኛው የአካባቢው ማህበረሰብ የመግቢያ በር ቀኝ በኩል ከሁለት አንዱ ወይም ሁለቱን የእጸዋት አይነት ተተክለው የሚገኙበት አጋጣሚ በጣም ብዙ መሆኑን ከተገኘው የቃል ማስረጃ በተጨማሪ በነበረ የመስክ ጊዜ ምልከታ (01-15/ 09/ 2016፣ ኩራር፣ 01-15/ 11/ 2016 ዓ.ም፣ ገልገሌ እና 16-30 /09/ 2016 ዓ.ም ምንጅ ቀበሌዎች) የበለጠ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ለዚህ ሀገረሰባዊ እምነት መኖርና መጠበቅ የተሰጡ ማህበራዊ ምክንያቶች እንደተጠበቁ ሆነው ነገር ግን በማህበረሰቡ ሀገረሰባዊ እምነት የዋንዛና የአንቃ ዛፎች እንዲተከሉ የሚፈለግ መሆኑ በተጠኘው አካባቢ የዋንዛና የአንቃ ዛፎች በብዛት እንዲገኙ ከማስቻል አኳያ የራሱ የሆነ ድርሻ ይኖረዋል ማለት ይችላል፡፡ የዋንዛና የአንቃ ዛፎች በብዛት እንዲተከሉና እንዲበቅሉ የሚበረታታ ከሆነ ደግሞ የተጠኘው አካባቢ ለጎርፍ፣ ለበረሃማነትና ለድርቅ ያልተጋለጠ በዛፎች የተሸፈነ የመሆን እድሉ ከፍተኛ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የተጠኘው አካባቢ የተስተካከለ አካባቢያዊ ስነ-ምህዳር እንዲኖረው ከማድረግ አንጻር የራሱ የሆነ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል ሊባል ይችላል፡፡ ይህን የሀገረሰባዊ እምነት ሚናም ‹‹ethnic adaptive folk traditions have played an important role in appraising many socio-ecological challenges›› (Biswas and Bain, 2022) በሚል በዘርፉ አጥኚዎች ስራ ውስጥ ተመላክቶ ይገኛል፡፡

## 4. መልካም ስብዕናን የማስተማር ሚና

ሀገረሰባዊ እምነቶች ማህበራዊ ግብረገብን ለማስተማር ይጠቅማሉ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈለጉ እና የማይፈለጉ ባህሪያትን በመግለጽ ሰዎች እንዴት መኖር እንደሚገባቸው ያስተምራሉ (Bascom, 1954) እንደሚለው የባለሙያ ሀሳብ የተወሰኑት ሀገረሰባዊ እምነቶች የማህበረሰቡ አባላት ከልጅነታቸው ጀምረው በመልካም ስብዕና የታነጹ እንዲሆኑ ከማድረግ አንጻር የራሳቸው ድርሻ ያላቸው ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

**አስረጅ፡- ከሰው ፊት አክታ መትፋት የማይገባ ስለመሆኑ**

በደጀን ወረዳ ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ እምነት ከሰው ፊት እንዲደረጉ ከማይፈቀዱ ነገሮች ውስጥ አንዱ ከሰው ፊት አክታ መትፋት ነው፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ አመለካከት ከአንድ ሰው ፊት አክታ መትፋት በማህበረሰቡ ውስጥ ሊኖር ከሚችል የቀደመ የእርስ በርስ ትውውቅ፣ ትስስርና ሰብአዊ ማንነት አንጻር በዋናነት ሁለት አይነት አሉታዊ ትርጉም እንደሚሰጠው ለማወቅ ተችሏል፡፡

የመጀመሪያው በሁለት ሰዎች (ቡድኖች ሊሆን ይችላል) መካከል በሚኖር ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ወዘተ ትስስር አማካኝነት ሊፈጠር የሚችል መቀያየም (ኩርፊያ)፣ ጥላቻ፣ የባላንጣነት ስሜት፣ ንቀት፣ ወዘተ ይኖራል፡፡ በዚህን ጊዜ አንደኛው ግለሰብ (ቡድን) ሌላኛውን እንደዚህ አይነት ስሜት በውስጡ ያለ መሆኑን በግልጽ ለማሳወቅ ሲፈልግ ሆነ ብሎ የሚያደርገው እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በቤተሰብ (በአሳዳጊ) በሰረዓት ተቀጥተው ያላደጉ ወይም ደግሞ በተፈጥሮ ሊመጣ በሚችል የባህርይ ችግር ምክንያት ለሰው ልጅ ክብርና ስሜት ሳይጠነቀቁ በአላዋቂ ድፍረት የሚፈጽሙት እኩይ ተግባር ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስለሆነም በማህበረሰቡ እምነት የባህርይ ችግር ያለባቸው ሰዎች አይነተኛ መለያ ተግባር ተደርጎ ይቆጠራል (አቶ ወለላው መርከቡ፣ ቄስ አየለ አለሙ፣ ወ/ሮ ታንጉት ቢተው እና ሌሎች፣ ቡድን ተኮር ውይይት፣ 09/09/ 2016 ዓ.ም፣ ኩራር)፡፡

በዚህም የተነሳ ከነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት ነገሮች ውጭ የሆነ ማንኛውም የማህበረሰቡ አባል እንደዚህ አይነት ሰብአዊ ፍረጃ ውስጥ ላለመካተት ሲባል፣ ይህን ‹‹የተነወረ›› ተብሎ የሚታሰበውን ተግባር ደፍሮ እንደማያደርግ ይናገራሉ፡፡ ይህ ማህበራዊ ሁኔታ ተፈጠረ ማለት ደግሞ በተዘዋዋሪ የአካባቢው ነዋሪዎች እርስ በራሳቸው መልካም ግንኙነት፣ መተሳሰብ፣ ፍቅር፣ መከባበር፣ አንድነት፣ ቅንነት፣ ወዘተ እንዲኖራቸው ከማድረግ አንጻር የራሱ የሆነ ድርሻ ይኖረዋል ማለት ይቻላል፡፡

## 5. ስነ-ልቡናዊ እረፍት የመፍጠር ሚና

እንደ Kabak (2025) ገለጻ ሀገረሰባዊ እምነት ለአንድ ማህበረሰብ ከሚሰጣቸው ፋይዳዎች ውስጥ አንዱ ስነ-ልቡናዊ መረጋጋት እንዲኖር ማስቻል ነው ይላሉ፡፡ ልክ በተመሳሳይ የደጀን ወረዳ ማህበረሰብ አንዳንድ ሀገረሰባዊ እምነቶችም የተጠኘውን ማህበረሰብ ስነ-ልቡና እረፍት እንዲያገኝ ሊያደርጉ የሚችሉ ሆነው ይታያሉ፡፡

**አስረጅ፡-የአድባር ድግስ ወደ መኖሪያ ቤት መወሰድ የሌለበት መሆኑ**

የአድባር ዛፍ በተጠኘው ማህበረሰብ እምነት በተፈጥሮ ከሌሎች ዛፎች በተለየ እራሱን፣ ማህበረሰቡን፣ አካባቢውን፣ ማህበረሰባዊ ሀብትና ንብረትን፣ ወዘተ ከክፉ ነገር መጠበቅና መከላከል የሚያስችል ተፈጥሯዊ ኃይል (ቆሌ) አለው ተብሎ ይታመናል፡፡

ከዚህም ጋር ተያይዞ የአካባቢው ህዝብ በአድባር ዛፉ ላይ ጥቃት እንዳይደርስ፣ ለተሰጠው ተፈጥሯዊ የመጠበቅና የመከላከል ኃይል ቆሌ መለማመኛ ዝግጅት (ማቋደሻ) ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ማድረግ የሚጠበቅ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ የሚደረገው ዝግጅትም ምንም እንኳን በሁሉም ቦታ ወጥነት ያለው ነው ለማለት ባይቻልም ነገር ግን ማህበረሰቡ አቅሙ በፈቀደው ልክ ብር በማዋጣትና ከቻሉ በሬ ወይም ላም ካልሆነ ግን ፍየል በመግዛት እርድ መፈጸም እንደሚገባ ይገልጻሉ፡፡

እያንዳንዱ ሰውም ዝግጅቱ የሚያስፈልገውን ያህል እንጀራ፣ ዳቦ፣ በርበሬ፣ ሽንኩር፣ ዘይት፣ ጠላ፣ እርጎ፣ ጠጅ፣ ብርዝ፣ ወዘተ ነገሮችን ይዞ ወደ አድባር ዛፉ ጥላ በመሰባሰብ ዝግጅቱን ይጀምራል፡፡ የተሰባሰበው የግብዣው ተሳታፊም ይዞት ከመጣው ወይም ደግሞ እዚያው አድባሩ ዛፉ ላይ ያዘጋጁትን ድግስ ሰው ከመቅመሱ በፊት ከየአይነቱ የአድባር ቆሌውን ማቋደስ ወይም ከአድባር ዛፉ እግር ወይም ግንድ ላይ ማፍሰስ የሚጠበቅ ጉዳይ ነው፡፡

ምክንያቱም በማህበረሰቡ እምነት ይህ ዝግጅት በሚደረግበት ወቅት የዛፉ ቆሌ በተሰብሳቢው ህዝብ መካከል በመሆን ቆሞ እስከሚሰጠው በጉጉት ይጠብቃል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚህን ሰዓት ለእሱ ሳይሰጥ በቅድሚያ የሚበላ ወይም የሚጠጣ ግለሰብ ወይም ቡድን ቢኖር ሊፈጠር በሚችል የቆሌው ብስጭትና ቁጣ ወዲያውኑ ይቀዘፋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ እንዳይሆን በመስጋት ተቀዳሚ ተግባራቸው የአድባሩን ቆሌን ማቋደስ ሊሆን ችሏል፡፡

በመጨረሻም የተዘጋጀው ምግብና መጠጥ ሲበላ፣ ሲጠጣ ከተዋለና ከተመሸ በኋላ የሚተርፍ ማንኛውም ምግብ ወይም መጠጥ ወደ ቤት ተመልሶ እንዲወሰድ አይፈቀድም፡፡ ወይ አድባር ዛፉ እግር ስር በክብር ይቀመጣል ወይ ደግሞ ከአድባሩ ስር ላይ በእርጋታ እንዲፈስ ይደረጋል፡፡

በአካባቢው ማህበረሰብ እምነት ይህ ተግባርና ክንውን የአድባር ዛፉን ቆሌ እንደማክበርና መንከባከብ አድርገው ከማሰብ ሻገር የአድባር ቆሌውን በከፍተኛ ሁኔታ የሚያስደስት ተግባር ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ በዚህም ምክንያት ማህበረሰቡ፣ የተጠኘው አካባቢ፣ የማህበረሰቡ ሃብትና ንብረት (ልጅ፣ ከብት፣ ሰብል፣ ቤት፣ ምርት፣ ብር)፣ ወዘተ ከማንኛውም ሰው ሰራሽ ወይም

ተፈጥሯዊ አደጋ በአድባር ቆሌው ንቁ ጥበቃ አማካኝነት አንዳች ክፉ ነገር ሳያዩ፣ ሳይሰሙ፣ ሳይደርስባቸውና ሳይነካቸው ዓመቱን በሙሉ እናሳልፋለን ብለው ይጠብቃሉ፡፡ እንዲሁም ያ አመት በሁሉም ነገር የስኬት፣ የሰላም፣ የፍቅር፣ የጥጋብ፣ የአንድነት ይሆናል ብለው ተስፋ ያደርጋሉ፡፡

ይህ ውስጣዊ ተስፋና የመሻት ስሜት ደግሞ የማህበረሰቡን ስነ-ልቡና እንዲረጋጋና እረፍት እንዲያገኝ ከማድረግ አኳያ የራሱ የሆነ ድርሻ ይኖረዋል ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ጉዳይ በተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ውስጥ ሀገረሰባዊ እምነቶች ሰዎች በሕይወታቸው ሊያጋጥማቸው የሚችሉ የፍርሃት፣ የጭንቀት ወይም ያልታወቁ ሁኔታዎችን ለመቀነስ እንደ ስነ-ልቡና ድጋፍ ያገለግላሉ (Malinowski, 1948) በሚል ይገለጻል፡፡

## 6. የሰብአዊነት ባህርይን የማጎልበት ሚና

ሰብአዊነት ማለት አንድ አካል (ቡድን) ክፉ ነገር እንዳይደርስበት ወይም ደግሞ ደርሶበትም ከሆነ ለመርዳት የምናሳየው ከፍተኛ የሆነ የርህራሄ፣ የሀዘኔታ፣ የመንከባከብ፣ የትብብርና የመልካም ባህርይ ስሜት መሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ፡፡ ልክ እንደዚህ ሁሉ ከዚህ በመቀጠል በማሳያነት የቀረበው ሀገረሰባዊ እምነትም በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ የሰብአዊነት ባህርይ እንዲጎለብት የራሱ የሆነ አበርክቶ አለው ማለት ይቻላል፡፡

**አስረጅ፡- ‹‹የመሸብኝ እንግዳ ነኝ አሳድሩኝ?›› ያለ ሰው የማይከለከል መሆኑ**

በደጀን ወረዳ ማህበረሰብ ውስጥ ‹‹የመሸበት እንግዳ›› ማለት ሳይጠበቅ፣ ሳይታሰብ፣ ካለቀጠሮ፣ ካለትውውቅ፣ ወዘተ በአጋጣሚ እርዳታ የሚጠይቅ ሰው ማለት ነው፡፡

በአካባቢው ህዝብ ሀገረሰባዊ እምነት እንደዚህ በአጋጣሚ የመጣን ማንኛውም ሰው (ዘመድ የሆነ ወይም ያልሆነ፣ የሚታወቅ ወይም እንግዳ) በእግዚያብሄር ፈቃድ የመጣና ቤት ውስጥ ማደር ብቻ ሳይሆን ቤት ካፈራው ምግብና መጠጥ እንዲካፈል የተፈለገ ሰው ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ ምክንያት ‹‹የእግዚያብሄር እንግዳ›› በሚል ይጠራል፡፡ ስለሆነም ካለምንም ማንገራገርና ማቅማማት በደስታ በመቀበልና አቅም በፈቀደ መጠን መንከባከብና ማስተናገድ እንደሚገባ ይናገራሉ፡፡ ይህ በመደረጉም በእንግዳ ተቀባዮች አስተሳሰብ በሚበሉት ምግብና በሚጠጡት መጠጥ ላይ የእግዜር መንፈስ ቅዱስ ስለሚያርፍበት ምግቡና መጠጡ የተባረከ እንደሚሆንና ባላቸው ቀሪ ሀብትና ንብረት ላይም ፈጣሪያቸው በረከቱንና ረድኤቱን ያበዛልናል ብለው እንደሚያምኑ ይገልጻሉ (አቶ ብርብራው ታለማ፣ ቃለ መጠይቅ፣ 12/ 09/ 2016 ዓ.ም፣

ምንጅ)፡፡ ቄስ ለይኩን አባይ (ቃለ መጠይቅ፣ 08/ 10/ 2016 ዓ.ም፣ ቆንቾር) የተባሉ ሌላኛው መረጃ አቀባየ ደግሞ እንግዳ ተቀባይነት በእግዚያብሄር እንደሚወደድ ለዚህም አብረሃም ያሳየውን እንግዶችን አክብሮ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ በፍጥነት በማዘጋጀቱ በእግዚያብሄር የተሰጠው ትልቅ ክብርና ቦታን በምሳሌነት በመጥቀስ አስረድተዋል፡፡

ይህ የማህበረሰቡ አስተሳሰብ ደግሞ በተጠኚው ማህበረሰብ መካከል ለሚኖረው የትህትና፣ የመተዛዘን፣ የመተሳሰብ፣ የመደጋገፍ፣ የመረዳዳት፣ ወዘተ ባህልና አመለካከት የዳበረ እንዲሆን ከማድረግ አንጻር የራሱ ድርሻ ይኖረዋል ማለት ይቻላል፡፡

## 7. ኢኮኖሚን የማሳዳግ ሚና

እንደ Kabak (2025) ያሉ አጥኚዎች ሀገረሰባዊ እምነቶች የማህበረሰብን ወይም ህዝብን ስኬታማነትና ብልጽግናን ከማረጋገጥ ባሻገር እራሳቸውን ከችግርና ከረሃብ እንዲከላከሉ ያግዛል፤ በማለት ሀገረሰባዊ እምነቶች ለሀገር ግንባታ ስኬት ያላቸውን ጠቀሜታ ያመለክታል፡፡ ልክ እንደዚህ ሁሉ አንዳንዶቹ የማህበረሰቡ ሀገረሰባዊ እምነቶች የተጠኚውን ማህበረሰብ ኢኮኖሚን ከማሳደግ አኳያ የራሳቸው ድርሻ አላቸው ሊባሉ የሚችሉ ናቸው፡፡

**አስረጅ፡- የህዳር አህያ የማይከለከል መሆኑ**

የህዳር ወር በአብዛኛው የተጠኚው አካባቢ የተሰበሰበው አዝመራ የሚወቃበትና የተወቃውን ሰብልም ከአውድማ ወደ ቤት የሚጓጉዙበት ወቅት መሆኑን ከዚህ በፊት ከነበረኝ ዳራዊ እውቀትና በቃለ መጠይቅ ባደረኩት ተጨማሪ ማረጋገጫ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ስለሆነም ይህ ወር በአካባቢው ማህበረሰብ ከፍተኛ የስራ ጫናና ጥድፊያ ያለበት ነው ሊባል ይችላል፡፡

በእርሻ ስራ የሚተዳደረው ማህበረሰብ ሁሉም በሚባል ደረጃ ሰብሉን ከአውድማ ወደ ተዘጋጀለት ማከማቻ ለማጓጓዝ በዋናነት አህያን አዘውትሮ የሚጠቀም ሲሆን፣ አልፎ አልፎ ግን ፈረስ፣ በቅሎ፣ በሰው ትክሻና ጀርባ፣ በጋሪና እስከተወሰነ ቦታ ድረስ ደግሞ በተሽከርካሪ መኪና እንደሚጠቀሙ ለማየትና ለመረዳት ተችሏል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ መረጃ ከሰጡኝ ሰዎች መካከል አቶ ዘሪሁን ታሪኩ (ቃለ መጠይቅ፣ 06/ 03/ 2017 ዓ.ም፣ ገልገሌ) እንደሚሉት፡-

> *የህዳር ወር ለሰው ልጅ የደም ስር የሆነው ሰብል ሜዳ ላይ (አውድማ ለማለት ነው) ተዘርሮ የሚውል የሚያድርበት ወቅት ነው፡፡ በአካባቢው አስተሳሰብ አውድማ ላይ እህል ከዋለ ካደረ የሰማይ (ዝናብ፣ በረዶ) ወይም የምድር (የለሊት አውሬ፣ የሰው ሌባ፣ ሰላቢ*

> *መንፈስ፣ ወዘተ) ችግር አያጣውም ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስለሆነም ገበሬው ሰብሉን በፍጥነት ወደ ቤቱ መሰብሰብ ይፈልጋል፡፡ ለመሰብሰብ ደግሞ ማንጓዣ ግድ ነው፡፡*
>
> *የአካባቢው ማህበረሰብም ይህንን ሁኔታ ስለሚያውቅ የተለያየ አማራጭን በመጠቀም ሰብሉን ለማንጓዝ ይሯሯጣል፡፡ በዚህን ጊዜ በተለያየ ምክንያት ሊሆን ይችላል የጭነት አገልግሎት የማትሰጥ ነጻ አህያ በመንገድ ላይ ያገኘ ማንኛውም ሰው ባለቤቱን ሳያስፈቅድ ይዞ በመሄድ ሲጭናት መዋል ይችላል፡፡ ባለቤቱ ስትጫን የዋለች መሆኑን፣ ማን እንደጫነት ቢያውቅም፣ የጫናትን ሰው ከነ አህያዋ መንገድ ላይ በአጋጣሚ ቢያገኘውም መጫኗም አይደንቀውም፤ ለምን እንደዚህ አደረክ ብሎም ሰውየውን አይጠይቅም፤ አይወቅስም፡፡ ምክንያቱም የማትከለከል ‹‹የህዳር አህያ ስለሆነች!›› በማለት ያስረዳሉ፡፡*

ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው ነገር በደጀን ወረዳ ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ እምነት እየተወቃ ያለ ሰብል አውድማ ላይ ከዋለ ካደረ ሰበብ አያጣውም ተብሎ የሚታመን መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም ካለ ምንም ችግር በቶሎ ወደ ተዘጋጀለት ጎተራ ወይም ቦታ እንዲወሰድ ይፈለጋል፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ በማህበረሰቡ ሀገረሰባዊ እምነት በዚህ ወር ውስጥ ጭነት ላይ ያልሆነች አህያ ማንም መንገድ ላይ ያገኛት መጫን የሚፈልግ ሰው ወስዶ ካለምንም መሳቀቅ፣ ፍራቻ፣ አድሎ፣ ክልከላና ቅሬታ በነጻነት መገልገል የሚችል መሆኑን እና በማህበረሰቡ ውስጥ አንዱ ለሌላው ያለው የተባባሪነት መንፈስ ከፍ ያለ መሆኑን ነው፡፡

ይህ የማህበረሰቡ የመረዳዳት፣ የመደጋገፍና የመተሳሰብ አዎንታዊ ባህል ደግሞ በአንድም ይሁን በሌላ የተወቃው እህል ለዝናብ፣ ለበረዶ፣ ለለሊት አውሬ፣ ለሌባ፣ ለሰላቢ፣ ወዘተ ችግር ሳይጋለጥና ምርቱ ሳይባክን በተሳካ ሁኔታ በፍጥነት ወደ ተዘጋጀለት ቦታ እንዲገባ ከማድረግ አኳያ የሚጫወተው ሚና ቀላል አይደለም፡፡ ይህ ሆነ ማለት ደግሞ በተዘዋዋሪ የተጠኘውን ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት (ምርታማነት) የተሻለ እንዲሆን ያግዛል ማለት ነው፡፡ ‹‹…folk belifes can not only innovate the development of traditional culture, but also, help the development of rural economy and promote the implementation of the rural revitalization strategy›› (Liu, 2023).

## 8. ማህበራዊ አንድነትና ትስስር እንዲጠነክር የማድረግ ሚና

የተወሰኑት ሀገረሰባዊ እምነቶች ደግሞ በተጠኘው ማህበረሰብ መካከል ጠንካራ አንድነት እንዲፈጠርና መልካም የሆነ የእርስ በርስ ትስስር እንዲኖር የሚያግዙ ናቸው ሊባል ይችላል፡፡ በተመሳሳይ ይህ ማህበራዊ ፋይዳ በተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ምልከታ ሀገረሰባዊ እምነቶችን እንደ ማህበራዊ መዋቅር አካል በመመልከት ለማህበረሰቡ አንድነት እና ስርዓት መጠበቅ እንደሚረዱ Radcliffe-Brown (1952) ይገልጻሉ፡፡

### አስረጅ፡- የግብዣ ጥሪን ማክበር ግድ መሆኑ

የደጀን ህዝብ በተለያየ ማህበራዊ አጋጣሚዎች በደስታ ጊዜ (በትምንምን፣ በሰርግ፣ በምላሽ፣ ወዘተ)፣ በበዓላት ቀን (እንቁጣጣሽ፣ ገና፣ ፋሲካ፣ ወዘተ)፣ በሀዘን ጊዜ (አርባ፣ ሰማኒያ፣ ተዝካር፣ ዓመታት ወዘተ) እና በሌሎችም ዓለማዊና መንፈሳዊ ይዘት አላቸው ተብለው በሚታሰቡ ዝግጅቶች ላይ በሚኖር ድግስ ዘመዱን፣ ወዳጁን፣ ባለውለታውን፣ ወዘተ ከደስታው ተካፋይ ወይም ከሃዘኑ ተጋሪ እንዲሆን በማሰብ ለግብዣ መጥራት የተለመደ ጉዳይ ነው፡፡

ስለዚህ ማንኛውም የአካባቢው ሰው ተከብሮ በቃል፣ በጽሁፍም ሆነ አሁን አሁን በስልክ ጭምር ለግብዣ (ድግስ) ከተጠራ ባልተጠበቀ ወይም ደግሞ በሌላ ከባድ ችግር ምክንያት ካልሆነ በስተቀር መቅረት የማይታሰብ ነገር መሆኑን ነው የሚናገሩት፡፡ ምክንያቱም እንደ መረጃ ሰጭዎች ማብራሪያ ከሆነ ማህበረሰቡ እነዚህን በተለያየ ወቅት፣ ቦታና ጊዜ በመጠበቅ የሚፈጽማቸው ዝግጅቶች ሲያደርግ በዋናነት ሁለት ነገሮችን ታሳቢ በማድረግ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ የመጀመሪያው በማህበረሰቡ እምነት የአንድ ዝግጅት መደረግ በግለሰብ፣ በቤተሰብም ሆነ በአካባቢ ደረጃ ያስገኛል ተብሎ የሚጠበቅ ስጋዊ ወይም መንፈሳዊ ጥቅም ለማሳካት በማቀድ የሚደረግ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የደጀን ወረዳ ህዝብ ይህንን የደስታ ወይም የሀዘን ይዘት ሊኖረው የሚችለውን ዝግጅት እንደ ሰበብ በማድረግ በቅርቡ ያሉ ሰዎችን ለምሳሌ፡- ቤተሰብ፣ ዘመድ፣ ወዳጅ፣ ባለውለታ፣ ወዘተ ጋር ያለውን የአፍም ሆነ የተግባር ትስስሮችን የእውነት ወዳጅ፣ የልብ አክባሪ፣ ቁም ነገረኛ የሆነውን ካልሆነው የሚለዩበት ስልት ጭምር መሆኑን ነው የታወቀው፡፡

ይህ ማህበራዊ ሀገረሰባዊ አስተሳሰብ ደግሞ ሰዎች ከሚሄዱበት ዋና ጉዳይ ባሻገር በግብዣ ጥሪ ሰበብ ከተሰባሰቡ ሌሎች አዳዲስ ሰዎች ጋር እንዲተዋወቁ፣ ከሚተዋወቁ ሰዎች ጋር ደግሞ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አካባቢያዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ወዘተ ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩ፣

እንዲነጋገሩ፣ እንዲመካከሩ፣ በጋራ እንዲወስኑ በር ይከፍታል፡፡ ይህ በተለያዩ አሰባሳቢ አውዶች እየተገናኙ የመተዋወቅ፣ የመነጋገር፣ የመወያየት፣ የመመካከር፣ የመጫዎት፣ ወዘተ ልማዳዊ እሴት ደግሞ በጊዜ ሂደት በተጠኝው ማህበረሰብ አባላት መካከል ጠንካራ ማህበራዊ አንድነትና ትስስር እንዲኖር ከማስቻል አንጻር የሚኖረው አበርክቶ ቀላል አይሆንም፡፡ ‹‹Community food events have the potential to display relations of cooperation, exchange, solidarity, and sometimes conflict within friendship and extended-kinship networks›› (Bauman, 1992).

## 9. ባህልን የማጽናትና የማስቀጠል ሚና

የባህል መለያ ባህሪያት ከሚባሉት መካከል አንዱ "Culture is dynamic and adaptive" (Louise, 2021) የሚለው ነው፡፡ ሀቁ ይህ ቢሆንም ቅሉ ተጠኝው ማህበረሰብ ግን በረጅም የህይወት ልምድና ተሞክሮ በፈጠራቸውና ባዳበራቸው ሀገረሰባዊ እምነቶች አማካኝነት የቆየውን ልማዳዊ አስተሳሰብና ተግባር በዘመን አፈራሽ አስተሳሰብና ተግባር በከፊል ወይም በሙሉ ሳይተኩ፣ ሳይበረዙና ሳይረሱ ለማቆየትና ለማስቀጠል ሲል የተለያዩ ማህበራዊ ምክንያቶችን በመጠቀም ጥረት የሚያደርግ መሆኑን ነው ማረጋገጥ የተቻለው፡፡ ለምሳሌ፡-ለነገሮች የሰናይ ወይም የእኩይ፣ የጠቃሚ ወይም የጎጅ፣ የትክክል ወይም የስህተት፣ ወዘተ ምንነትና ፀባይ በማላበስና በመስጠት ጥረት እንደሚያደርግ ለማወቅ ተችሏል፡፡

### አስረጅ፡-ምግብና መጠጦች መበላትና መጠጣት ያለባቸው በቀኝ እጅ ብቻ መሆኑ

የደጀን ወረዳ ማህበረሰብ በእለት ከእለት ህይወቱ ወይም ደግሞ ቀናትን፣ ወራትን ብሎም ዓመታትን ጠብቆ ለሚያከናውናቸው ዓለማዊ ወይም መንፈሳዊ ዝግጅቶች የሚሆኑ የተለያዩ ምግቦችንና መጠጦችን የሚያዘጋጅ ህዝብ ነው፡፡ ሆኖም ግን በእየለቱ ወይም ወቅትና ጊዜን ጠብቀው የሚያዘጋጇቸውን ምግብና መጠጦች እንደፈለገ በዘፈቀደ የሚበሉና የሚጠጡ ሳይሆን በተጠኝው ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ እምነት አማካኝነት የተቀመጡ ማህበራዊ እሴቶችን በአከበረ መልኩ ነው፡፡ ከማህበራዊ እሴቶች መካከል ‹‹ምግብና መጠጦች መበላትና መጠጣት ያለባቸው በቀኝ እጅ ብቻ መሆኑ›› የሚለው አንዱ ነው፡፡

ይህ የማህበረሰቡ አስተሳሰብና ተግባር ተቀባይነት እንዲኖረው፣ እንዲቀጥልና እንዲፀና ደግሞ በቀኝ እጅ የተበላና የተጠጣ ነገር ያጠግባል፤ በሆድ ይረጋል፣ ጤናማ ያደርጋል ይላሉ፡፡ በግራ እጅ የተበላ ምግብና መጠጥ ደግሞ በተቃራኒው አያጠግብም፤ ከተበላ በኋላም ተመልሶ ሊወጣ ይችላል፤ ለጤናም አይመችም የሚል ማህበራዊ ምክንያት ያቀርባሉ፡፡ ይህ የሀገረሰባዊ እምነት

ፋይዳ ለመጠቆም ሀገረሰባዊ እምነቶች ባህላዊ እሴቶችን ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ ለማስተላለፍ ዋና መንገድ ይሆናሉ። በዚህ መሠረት ሀገረሰባዊ እምነቶች የህዝብ ልማዳዊ ልምዶችን፣ እሴቶችን፣ እና አመለካከቶችን በማስቀጠል የባህል ቀጣይነትን ያረጋግጣሉ (Malinowski, 1948; Dundes, 1980) በሚል በዘርፉ ምሁራን ተገልጾ ይገኛል።

## 10.ጠንካራ ስብዕና የመፍጠር ሚና

ተጠኚው ማህበረሰብ በየትኛውም የእድሜ ደረጃ ላይ የሚገኝ የማህበረሰቡ አባል በአካልም ሆነ በሌላ ነገር ጠንካራ ስብዕና ያለው ሰው እንዲሆን ይፈልጋል። ለዚህ አይነት ሰብዕና መቅረጫነት ደግሞ ሀገረሰባዊ እምነቶችን እንደ መሳሪያ እንደሚጠቀም ከተገኘው መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል። ሀገረሰባዊ እምነቶች ለማህበረሰብ ከሚሰጡት ተግባራዊ ፋይዳ መካከል አንዱ ጠንካራ ስብዕና መገንባት ነው (Kabak, 2025) የሚለው የባለሙያ ሀሳብም ሌላኛው ማሳያ ነው።

### አስረጅ፡-ምግብ እየተበላ ውሃ መጠጣት የማይቻል መሆኑ

በማህበረሰቡ ውስጥ ሲወርድ ሲወራረድ በተገኘ ጥበብና እውቀት ተዘጋጅተው ጥቅም ላይ የሚውሉ የተለያዩ የምግብና የመጠጥ ዓይነቶች እንደሚገኙ፣ ከሚጠቀሙበት የጊዜ እርዝመት አንጻር ደግሞ የዘወትርና የአልፎ አልፎ ተብለው በሁለት ሊከፈሉ እንደሚችሉ ከተገኘው የጥናት መረጃ ለማወቅ ተችሏል።

እንደ አካባቢው ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ እምነት እነዚህን ምግቦች በሚመገቡበት ጊዜ ማንኛውም ለአቅመ አዳም (ሄዋን) የደረሰ የማህበረሰቡ ወንድም ሆነ ሴት አባል በመሃል አቋርጦ ውሃ ወይም ሌላ የተዘጋጀ ፈሳሽ መጠጥ (ጠላ፣ እርጎ፣ ቡቅር፣ ጠጅ፣ ብርዝ፣ ወዘተ) መጠጣት አይችልም። መጠጣት የሚቻለው ወይ ከምግብ በፊት ወይም ደግሞ ከምግብ በኋላ መሆን እንደሚገባው ይናገራሉ። ምክንያቱም በማህበረሰቡ እምነት አንድ ሰው በተለይ ወንድ ልጅ በምግብ መሃል እያቋረጠ አስር ጊዜ ውሃ ወይም ሌላ ነገር የሚጠጣ ከሆነ ችግርና መከራን መቆቋምና ማለፍ የሚችል ምራቅ የዋጠ ወንድ አይሆንም ተብሎ ይታሰባል። እንዲሁም ወንድ ልጅ ነገ ምን እንደሚገጥመው ስለማይታወቅ ቆፍጣና ሰው መሆን አለበት ይላሉ። ቆፍጣና ለመሆን ደግሞ እንደተባለው በምግብ መሃል ውሃ ወይም ሌላ ፈሳሽ ነገር መጠጣት የለበትም ብለው ያምናሉ (አቶ አማረ አያሌው፣ቃለ መጠይቅ፣ 06/ 11/ 2016 ዓ.ም፣ ገልገሌ)።

ይህ የማህበረሰቡ አስተሳሰብና ተግባር ደግሞ ምግብ እየተበላ ሊኖር የሚችልን ውሃ ወይም ሌላ ፈሳሽን የመፈለግ ስሜት፣ የውሃ ጥም፣ የውሃ ጥገኝነት፣ መጠነኛ መታነቅ ተቋቁሞ ካለምንም

ፈሳሽ መመገብ መቻልን የሚያለማምድ ነው፡፡ ይህን አይነት ልምድ ማዳበር መቻል ደግሞ በህይወት ዘመናቸው ሊያጋጥማቸው ለሚችል የውሃ ወይም መሰል ነገሮች እጥረት ሳይንበረከኩና ሳይሸነፉ በማንኛውም ቦታና ጊዜ ሁሉንም ነገር ተቋቁመው ካለምንም የጥገኝነት ችግር መመገብ እንዲችሉ ከማድረግ አኳያ የሚጫወተው ሚና ቀላል አይሆንም፡፡

**11.የስራ ክፍፍልን የማስተማር ሚና**

የደጀን ማህበረሰብ እንደማንኛውም ማህበረሰብ ሁሉ በእለት ከእለት ወይም አልፎ አልፎ የሚያከናውናቸው በርካታ ተግባራት አሉት፡፡ እነዚህን ተግባራት ደግሞ ማንኛውም የማህበረሰቡ አባል በዘፈቀደ የሚፈጽማቸው ሆነው አልተገኙም፡፡ በመሆኑም የአካባቢውን የሀገረሰባዊ እምነት ህግና እሴቶችን በአከበረ መልኩ የሚፈጸሙ ናቸው፡፡ በዚህ የተነሳ አንዳንዶቹ የተጠኘው ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ እምነቶች በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን የስራ ድርሻ የሚያስተምሩ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

**አስረጅ፡-እርድ የሚፈጸመው በወንድ ብቻ መሆኑ**

የደጀን ወረዳ ማህበረሰብ ለተለያየ ዓላማና ግብ ሲል በተለያየ ጊዜና ወቅት ለእርድ የሚሆኑ እንስሳትን በአካባቢው ሃይማኖት፣ ወግና ልማድ መሰረት የሚፈጽም መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ማህበረሰቡ በረጅም ጊዜ ልምድና እውቀት የዳበረ ትክክል ነው ተብሎ የሚታሰብ ጾታን መሰረት ያደረገ የእርድ አፈጻጸም ስረዓት አለው፡፡ ስለሆነም በተጠኘው ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ እምነት እርድ መፈጸም ያለበት በወንድ ብቻ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ *‹‹ሴት ልጅ ለእርኩስ መንፈስ በቀላሉ ተጋላጭ ስለሆነችና በእርድ ቦታ ላይ ደግሞ እርኩስ መናፍስት ስለማይጠፉ ለዚያ እንዳትጋለጥ በማሰብ ነው፡፡››* (አቶ ዘሪሁን ታሪኩ፣ ቃለ መጠይቅ፣ 07/ 11/ 2016 ዓ.ም፣ ገልገሌ) በማለት ለምን እንደማይፈቀድ ያስረዳሉ፡፡

ሌሎቹ መረጃ ሰጭዎች ደግሞ ሴት ልጅ በተፈጥሮዋ ከላይ እንደተጠቀሰው መሆኗን ይጠቅሱና በዚህ የተነሳ እርድ ማረድ ብቻ ሳይሆን እንደ ወንዶች የሃይማኖት መሪ (ዲያቆን፣ ቄስ፣ መርጌታ፣ ጳጳስ፣ ወዘተ) መሆን፣ ከጎተራ (ጎታ) ገብታ እህል ማውጣት፣ እርሻ ማረስ፣ ወቅ መውቃት፣ ማበራየት፣ ወዘተ እንደማትችል ጭምር ይናገራሉ (አቶ ጌትነት ውቤ፣ ቃለ መጠይቅ፣ 12/ 09/ 2016 ዓ.ም፣ ደጀን ከተማ 01 ቀበሌ)፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ቤት ማጽዳት፣ ሊጥ ማቡካት፣ እንጀራ መጋገር፣ ወጥ መስራት፣ ጠላ መጥመቅ፣ ጠጅ መጣል፣ ቡና ማፍላት፣አረቂ ማውጣት፣ ልብስ ማጠብ፣ ህጻን መንከባከብ፣ ወዘተ የሴት ተግባራት ተደርገው

መታሰባቸው ነው (ወ/ሮ ፈንታነሽ አስማማው፣ ቃለ መጠይቅ፣ 20/03/ 2017 ዓ.ም፣ አቃቤት እና አቶ ጌትነት ውቤ፣ ቃለ መጠይቅ፣ 12/ 09/ 2016 ዓ.ም፣ ምንጅ እና ሌሎች)፡፡

እነዚህ ጾታ ነክ ሀገረሰባዊ እምነቶች መረጃ አቀባዮች ያደጉበትን ባህል፣ ወግ፣ አስተሳሰብ፣ እምነት፣ ወዘተ ነገሮችን መነሻ በማድረግ ከሰጧቸው ዝርዝር የቃል ማብራሪያዎች ባሻገር በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ የወንድና የሴት የስራ ድርሻ ምን እንደሆነ ለይተው የሚያሳዩና የሚያሳውቁ ሀገረሰባዊ እምነቶች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

### 12. ታማኝነትን የማስተማር ሚና

የተወሰኑት የማህበረሰቡ ሀገረሰባዊ እምነቶች ደግሞ ታማኝነትን የማስተማር ሚና ያላቸው ናቸው ሊባል ይችላል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የቀረበው ማህበረሰባዊ ተግባርና አስተሳሰብም ለዚህ አስረጅ ነው፡፡

**አስረጅ፡-ለቤተ-ክርስቲያን የተገባ ቃል (ስለት) መፈጸም ግድ ስለመሆኑ**

ማህበረሰቡ በእለት ከእለት እንቅስቃሴው፣ የወደፊት ህይወቱ በሁሉም ዘርፍ የተሳካ እንዲሆንለት ይመኛል፡፡ እነዚህን የእለት ፍላጎቶችና የወደፊት መሻቶች ደግሞ በስራ ብቻ ይመጣሉ ተብለው አይታሰቡም፡፡ ከጥረት በላይ የሌሎች አጋዥ ናቸው የሚባሉ አካላት መልካም ፈቃድና እገዛ ወሳኝ እንደሆነ አበክረው ይናገራሉ፡፡ የእነሱን እገዛ ለማግኘት ደግሞ እኛም በአቅማችን ሳንሰስት ለእነሱ የክብር መገለጫና መታመን የሚሆን ነገር ማድረግ ይጠበቅብናል ብለው ያምናሉ፡፡ እሱንም የተገባ ቃል (ስለት) ብለው ይጠሩታል፡፡ ቃል መግባት (ስለት) በተለያዩ ቤተሰባዊና ማህበራዊ አሰባሳቢ ዝግጅቶች (እንቁጣጣሽ፣ መስቀል፣ ፋሲካ፣ አድባር ድግስ፣ ወዘተ) ላይ አልፎ አልፎ ሊኖር የሚችል ቢሆንም ቤተ-ክርስቲያን በመሄድ ቃል የመግባቱ ሁኔታ ግን በጣም የተለመደና ዘወትራዊ ተግባር እንደሆነ ያስረዳሉ (ቄስ አየለ አለሙ፣ ቃለ መጠይቅ፣ 03/ 09/ 2016 ዓ.ም ኩራር እና ወ/ሮ ብርቱካን አለሙ፣ ቃለ መጠይቅ፣ 05/ 12/ 2016 ዓ.ም፣ ደጀን ከተማ 01 ቀበሌ)፡፡

በተጠኘው ማህበረሰብ እምነት ሲፈልጉት ወይም ሲመኙት የነበረ ነገር ተሳክቷል ተብሎ ከታመነ ወይም ደግሞ ፈርተውት የነበረ ነገር (የገጠማቸው ችግር) አልፈነዋል ብለው ካመኑ የተገባው የገንዘብ፣ የቁሳቁስ ወይም የሌላ ቃል (ስለት) የግድ መፈጸም ያለበት መሆኑን ያምናሉ፡፡ ካልሆነ ግን በማህበረሰቡ ሀገረሰባዊ እምነት ቃላቸውን ያልጠበቁለት ቤተ-ክርስቲያን

(በእነሱ አጠራር ታቦት) ከሃዲ መሆናቸውን ለማሳየትና በቀጣይም እንደዚህ አይነት ቅጥፈት እንዳይለመዳቸው ለማስተማር ሲል ሊገመት ለማይችል ችግር ያጋልጠናል ብለው ያስባሉ፡፡

ይህ ሀገረሰባዊ አስተሳሰብና ተግባር ደግሞ የተጠኘውን ማህበረሰብ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ለሚገባው ቃል ታማኝ የመሆንን ስብዕና እንዲላበስ ከማድረግ አንጻር የሚኖርው አበርክቶ ቀላል አይሆንም፡፡

### 13.ሳይንስና ቴክኖሎጅ እድገትና ሽግግር እንዲያመጣ የማድረግ ሚና

አንዳንዶቹ የማህበረሰቡ ሀገረሰባዊ እምነቶች ደግሞ ለሳይንስና ቴክኖሎጅ እድገትና ሽግግር እንዲያመጣ አስተዋጽኦ ያላቸው ይመስላሉ፡፡ ምክንያቱም ‹‹folklore is formed by the transfer of certain knowledge from generation to generation and ultimately can represent both a completed creative work and its makings›› (Babamuradova, 2022) በመሆኑ ነው፡፡

**አስረጅ፡-ዘመድ የማይጋባ ስለመሆኑ**

የደጀን ማህበረሰብ ጋብቻ ከማይጋባቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ አንዱ ዘመድ መሆን ነው፡፡ ማህበረሰቡ ዘመድን የስጋና የሌላ በማለት ይለያል፡፡

የስጋ ዘመድ ብሎ የሚያስበው ከወንድም እህት ጀምሮ እስከ ሰባት ቤት (ልጅ፣ አባት/ እናት፣ አያት፣ ቅድመ አያት፣ ቅም አያት፣ ቅማንት፣ ሽማት፣ ወዘተ) ትውልድ ያለውን እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ የዘር ቆጠራውም በእናትም በአባትም በኩል ያለውን የሁለት የስጋ ዘመድ (bilateral descent) የሚያካትት መሆኑን ነው ማረጋገጥ የተቻለው፡፡ የሌላ የሚሉት ደግሞ የስጋ ዝምድና ሳይኖር ክርስትና አባት ወይም እናት በአካባቢው አጠራር ‹‹አበልጅ›› በመሆን የሚፈጠርን የዝምድ አይነት ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ መረጃ ከሰጡኝ ሰዎች መካከል ቄስ ለይኩን አንዱ ናቸው፡፡ እንደ እሳቸው ገለጻ ከሆነ ‹‹ዘመድ በብሉይ ኪዳን ዘመን ስጋዊ ዝምድና ያለው ሲሆን የቅርብ ዘመዶች እንዳይጋቡ ተከልክሏል፡፡ በሀዲስ ኪዳን ግን ቃሉ የቅርብ ዘመድን ወይም ጠቅላላውን ወገን ሊያመለክት ይችላል›› (ቄስ ለይኩን አባይ፣ ቃለ መጠይቅ፣ 08/ 10/ 2016 ዓ.ም፣ ቆንቾር) በማለት በብሉይ ኪዳን ዘመን ወይም ክርስቶስ ከማሪያም ከመወለዱ በፊት የዝምድና ጽንስ ሀሳብ የስጋ ዝምድና ብቻ እንደነበርና በብሉይ ኪዳን ወይም በሌላ አገላለጽ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ከማሪያም ከተወለደና ጥምቀትን እራሱ በመጠመቅ ካስጀመረ በኋላ ግን ጽንስ ሀሳቡ ከስጋ ዘመድ ባለፈ በተለያየ መንገድ (የክርስትና እናት ወይም አባት ‹‹አበልጅ በመሆን››) የሚመሰረቱ ዝምድናዎችን

እንደሚጨምር ያስረዳሉ፡፡ በዚህ ምክንያት በማህበረሰቡ እምነት በእነዚህ የስጋና የመንፈስ ሁለት ወገኖች መካከል ምንም አይነት ጋብቻ እንዲኖር አይፈቀድም፡፡ ነገር ግን የተቀመጠውን የማህበረሰብ ህግ በመተላለፍ ዘመድ ከተጋባ በማህበረሰቡ ሀገረሰባዊ እምነት ጤናማ ሰው ሳይሆን ያልተለመደ አካላዊ ቅርጽ፣ ቀለም፣ መጠን፣ ቁጥር፣ ወዘተ ያለው ፅንስ ሊወለድ እንደሚችል ይገልጻሉ፡፡ በእነሱ አባባል ‹‹ጉድ ይወለዳል›› ተብሎ ይታመናል፡፡

ይህንን ጉዳይ ምሁራን ‹‹Incest is wrong›› (Mundy-Castle and Bundy, 2013) በማለት ይገልጹታል፡፡ ይህ የማህበረሰቡ አገላለጽና ማብራሪያ ከዘመኑ የሳይንስ ጥናት ምልከታና ውጤት አንጻር እንዴት ይታያል? ስለዘመድ ጋብቻስ (Consanguineous Marriage) ሳይንስ ምን ይላል?፣ የሚለውን ጥያቄ ስንፈትሽ ምንም እንኳን ተጠኝው ማህበረሰብ የሚሰጠው ማብራሪያ ከዘመኑ የሳይንስ ጥናት ደርሽበታለሁ ከሚለው አመክኒዮ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ባይገኝም ቅሉ ነገር ግን የዘመድ ጋብቻ በሳይንስ የጥናት ውጤት ጭምር ሳይቀር የማይደገፍ ተግባር ሆኖ መገኘቱ ነው፡፡ ይህ የውጤት ተመሳስሎ ደግሞ ማህበረሰቡ በራሱ መንገድም ቢሆን የስነ-ህይወት የዘረ-መል (genetics) እውቀትን አስቀድሞ የተረዳና ያወቀ መሆኑን የሚጠቁም ይመስላል፡፡ ምክንያቱም በስነ-ህይወት የዘረ-መል (genetics) ጥናት ጤናማ የሆነ ጽንስ የሚፈጠረው የሴትና ወንድ ‹‹xx›› እና ‹‹xy›› ‹‹ክሮሞዞም›› በሚፈለገው ቁጥር ልክ ተመጣጣኝ ሆኖ ሲገኝ መሆኑን የዘረ-መል አጥኝዎች ያስረዳሉ፡፡ ነገር ግን መሆን ካለበት ‹‹የክሮሞዞም›› ቁጥር (46) በላይ ወይም በታች ከሆነ ያልተለመደ አካላዊ ቅርጽ፣ ቀለም፣ መጠን፣ ቁጥር፣ ወዘተ ያለው ፅንስ ሊወለድ እንደሚችል ይገልጻሉ፡፡ ለዚህ አይነት ‹‹የክሮሞዞም›› መዛባት መንስኤ ሊሆኑ ከሚችሉ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ደግሞ የስጋ ዝምድ (Consanguineous Marriage) ወይም የተቀራረበ ዘረ-መል ባላቸው ባልና ሚስቶች ላይ እንደሆነ ተመላክቷል (Heidari, Dastgiri, Akbari, Khamnian, Khanlarzadeh, Baradaran, Jabbary-Fam, Badrazar, Heidarzadeh, Tajaddini, 2014)፡፡

ስለዚህ በማህበረሰቡ ሀገረሰባዊ እምነት ዘመድ አይጋባም የሚሉበት ምክንያት በተዘዋዋሪም ቢሆን ይህንን የዘረ-መል መዛባት የሚያመጣውን ጣጣ አስቀድመው በመረዳታቸው ነው ሊባል ይችላል፡፡ ከዚህ አንጻር ይህ የቆየ የማህበረሰቡ ልማዳዊ አስተሳሰብና እውቀት ለዘመናዊው የዘረ-መል (genetics) ሳይንስ ጥናትና እድገት እንደ መነሻ መሰረት ሆኖ ያገለገለ ይመስላል፡፡

## 14.ግልጸኝነትን የማስተማር ሚና

ሀገረሰባዊ እምነቶች ለአንድ ማህበረሰብ ወይም ህዝብ ከሚሰጡት በርካታ ተግባራዊ ፋይዳዎች መካከል ግልጸኝነት አንዱ ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም ከመስክ የተሰበሰቡ የተወሰኑት የጥናት መረጃዎች ግልጸኝነትን የማስተማር ሚና ያላቸው ሆነው በመገኘታቸው ነው።

**አስረጅ፡-ሴት ልጅ ባል ካገባች እለት ጀምሮ መቀነት መታጠቅ የሚገባ ስለመሆኑ**

በደጀን ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ እምነት ሴት ልጅ ሳታገባ ማድረግ የማትችለው፣ ነገር ግን ካገባች በኋላ ደግሞ ማድረግ የሚጠበቅባት ነገር ቢኖር መቀነት መታጠቅ ነው። መቀነት በአካባቢው በሚኖር ሽማኔ ልማዳዊ አሰራር ጥበብ አማካኝነት ከጥጥ በሚዘጋጅ ፈትል ብዙን ጊዜ ከጫፍና ጫፍ ላይ የተለያየ ቀለም ባላቸው ክሮች የሚሰራ የአንገት ልብስ መሳይ የሴቶች የወገብ መታጠቂያ ባህላዊ ልብስ ነው።

በተጠኘው አካባቢ አንድ ሴት የመጀመሪያ ባል (በአካባቢው አጠራር አሚን) ካገባች እለት ጀምሮ ትዳሩ ቢቀጥልም ባይቀጥልም፣ ባል ቢኖርም ባይኖርም እስከ ህይወቷ ፍጻሜ ድረስ የምታደርገው እንደሆነ ይናገራሉ። ይህ የሚሆንበት ማህበራዊ ምክንያት ደግሞ መቀነት የታጠቀች ሴት፡- ልጃገረድ ያልሆነች መሆኗን የምታሳውቅበት (ወንድ የቀመሰች መሆኑን የምታሳይበት)፣ ከልጅነት የእድሜ ደረጃ ወደ ወጣትነት የተሸጋገረች በመሆኑ ብቻዋን ሳይሆን ከወንድ ጋር አብራ የምትኖር ባለ ትዳር መሆኗን የምታውጅበት፣ ወይም ደግም አግብታ የፈታች መሆኗን የምታሳውቅበት፣ ለአቅመ ሄዋን የደረሰች በመሆኗ ከቤተሰቧ ተለይታ ባል በማግባት በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ ትስስር እራሷን ችላ ቤት መምራት የምትችልበት እድሜ ላይ ያለች ሴት (ሁለንተናዊ ኃላፊነት በራሷ አቅም መሸከም የምትችል) መሆኗን ለማህበረሰቡ በይፋ መልዕክት የምታስተላልፍበት አካባቢያዊ ልብስ በመሆኑ እንደሆነ ይናገራሉ (አቶ ብርብራው ታለማ፣ ቃለ መጠይቅ፣ 12/ 09/ 2016 ዓ.ም፣ ምንጅ)።

ነገር ግን ከትዳር በኋላ መቀነት የማትታጠቅ ሴት የምትኖር ከሆነ በተጠኘው ማህበረሰብ እምነት በግብሯ ስነስረዓት የሌላት፣ ባህሪያዊ ማንነቷ ደግሞ ሞኛ ሞኝ የሆነችና ቁም ነገር የሌላት ሴት ተደርጋ የምትታሰብ በመሆኑ በአካባቢው ማህበረሰብ የተናቀች እንደምትሆን ያስረዳሉ። በአንጻሩ ደግሞ ባል ሳታገባ መቀነት የምትታጠቅ ሴት ደግሞ ከማህበረሰቡ የጋብቻ ወግና ልማድ ባፈነገጥ መልኩ ባል ማግባት እፈልጋለሁና ዳሩኝ የሚል መልዕክት እንዳስተላለፈች ተደርጎ ስለሚታይ በአካባቢው ማህበረሰብ እዩኝ እዩኝ ባይ፣ ደረስኩ ባይ ወይም በእነሱ አጠራር ‹‹ሳይሞቅ ፈላ›› በማለት እንደምትሰደብና እንደምትሸሞር ይናገራሉ።

ይህ የተጠኘው ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ አለባበስ ደግሞ ለአካባቢው ነዋሪዎች ከሚያስተላልፈው መልዕክት ባሻገር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በማህበረሰቡ ውስጥ ግጸኝነትን ከማስተማር አንጻር የሚኖረው ፋይዳ ቀላል አይሆንም፡፡

## 15.መከባበርን የማስተማር ሚና

ሌላኛው የተጠኘው ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ እምነቶች ሚና ደግሞ መከባበርን የማስተማር ነው ሊባል ይችላል፡፡

**አስረጅ፡- በአንቱታ መጥራት የሚጠበቅ መሆኑ**

‹‹አንቱታ›› በተጠኘው ማህበረሰብ እምነት ለሆነ ሰው (የማህበረሰብ ክፍል) ከማንኛውም ሰው በተለየ በእድሜ አዛውንት የሆኑ፣ በማህበራዊ ደረጃ፣ በጋብቻ፣ ወዘተ ምክንያት ልዩ ቦታ፣ ክብርና አድናቆት ያላቸው መሆኑን ለማሳወቅ ሲባል በንግግር ወቅት የሚጠቀሙት የማክበሪያ ቃል ነው፡፡

በእድሜ አዛውንት የሆኑ ሰዎች ሲባል በማህበረሰቡ ውስጥ በአማካኝ ከስልሳዎቹ የእድሜ ክልል በላይ የሚገኙ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ባልቴቶች፣ የቆረቡ፣ የመነኮሱ፣ ወዘተ ሰዎችን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡

በማህበራዊ ደረጃ ልዩ ስፍራ የሚሰጣቸው ሰዎች ሲባል ደግሞ ለምሳሌ፡-በቤተ-ክህነት (ቄስ፣ መርጌታ፣ ደብተራ፣ ኤጲስ ቆጶስ፣ ጳጳስ ወዘተ)፣ ልዩ ተፈጥሯዊ ፀጋ አላቸው ተብሎ የሚታሰቡ ሰዎች (ጠንቋይ፣ ሙት አናጋሪ፣ ወዘተ)፣ በዘመናዊ ትምህርት ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ ሰዎች (ለምሳሌ፡-ዶክተሮች፣ ኢንጅነሮች፣ ፖይለቶች፣ ተመራማሪዎች፣ ወዘተ)፣ ባለጸጋ፣ የሀገር ባለውለታ፣ ባለጀብድ፣ ወዘተ የሆኑ ሰዎችን ሁሉ የሚያመለክት ነው፡፡

በጋብቻ የተሳሰሯቸው ማለት ደግሞ የባል ወይም የሚስት ቤተስብና የቅርብ ዘመዶች በአጠቃላይ የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ሀገረሰባዊ እምነት ሴት ልጅ ባል ከአገባች ዕለት ጀምሮ እስከ ዕለተ ሞት ድረስ ትዳሩ ጸንቶ እስከ መጨረሻው ቀጠለም አልቀጠለም የባሏን እናትና አባት፣ ከባሏ እድሜ በላይ የሆኑ ወንድሞችና እህቶችን፣ እንዲሁም የቅርብ ዘመዶችን በሙሉ ‹‹በአንቱታ›› መጥራት የሚጠበቅና የተለመደ ነገር መሆኑን ነው የሚናገሩት፡፡ ወንድ ልጅም በተመሳሳይ ሚስት ከአገባ ዕለት ጀምሮ እስከ ዕለተ ሞት ድረስ ትዳሩ ጸንቶ እስከ መጨረሻው ቀጠለም አልቀጠለም የሚስቲቱን እናትና አባት፣ ከሚስቲቱ እድሜ በላይ የሆኑ ወንድሞችና እህቶችን፣ እንዲሁም የቅርብ ዘመዶችን በሙሉ ‹‹በአንቱታ››

*መጥራት የሚጠበቅ ማህበራዊ ግዴታ መሆኑን ነው የሚናገሩት* (አቶ ጌትነት ውቤ፣ *ቃለ መጠይቅ*፣ 12/ 09/ 2016 *ዓ.ም*፣ ምንጅ)። *አያይዘውም እነዚህን የማህበረሰብ ክፍሎች ክብር ሰጥቶ ‹‹በአንቱታ›› መጥራት በማህበረሰቡ ሀገረሰባዊ እምነት እድሜ፣ ጤናና ሲሳይ (እንጀራ) ያስገኛል ተብሎ ከመታሰቡ በተጨማሪ የጨዋ ሰው ምልክትና መለያ ባህርይ እንደሆነ ተደርጎ ይታመናል። በተለይ ግን በጋብቻ መልክ የሆነ ትስስር ከሆነ ደግሞ የሚጠበቅ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ጭምር መሆኑን ነው አጽንኦት ሰጥተው የሚያስረዱት።*

*ስለሆነም እነዚህ እድሜን፣ ማህበራዊ ደረጃንና የጋብቻ ሁኔታን መነሻ በማድረግ ተግባራዊ የሚደረጉ ማህበራዊ እሴቶች ያስገኙታል ተብሎ ከሚታሰበው ጥቅምና ከሚያስተላልፉት ባህሪያዊ መልዕክት ባሻገር በተጠኚው ማህበረሰብ አባላት መካከል አንደኛው ሌላኛውን ማክበር ማህበራዊ የውዴታ ግዴታ መሆኑን የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ከማድረግ አኳያ የሚጫዎቱት ሚና አዎንታዊ ነው ሊባል ይቻላል። በዚህ ምክንያት በተጠኚው ማህበረሰብ ውስጥ መከባበር እንዲጎለብት የሚያግዙ ናቸው ማለት ይቻላል።*

### 16. ተጠያቂነትን የማስተማር ሚና

*የተወሰኑት የተጠኚው ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ እምነቶች ደግሞ ተጠያቂነትን የማስተማር ሚና ያላቸው መሆኑን ነው መናገር የሚቻለው።*

**አስረጅ፡-ለክርስትና ልጅ ህብስት ዳቦ መውሰድ ግድ መሆኑ**

*በአካባቢው ማህበረሰብ ዝምድና ከሚመሰርትባቸው መንገዶች* (ጋብቻ፣ የነፍስ አባትና ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ተቋማት) *ውስጥ አንዱ የክርስትና ልጅ ማድረግ ወይም በእነሱ አጠራር ‹‹አበልጅ መናሳት›› ነው። ተጠኚው ማህበረሰብ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተከታይ እንደመሆኑ ህጻን በተወለደ ወንዱን በአርባ ቀን፣ ሴት ከሆነች ደግሞ በሰማኒያ ቀን ክርስትና ማስነሳት ግዴታ ነው። ምክንያቱም በአካባቢው ማህበረሰብ እምነት ክርስትና ማስነሳት ማለት ሃይማኖት አልባ የነበረው ህጻን አማኝ ሆነ፣ የተቀደሰ ሆነ፣ የሃይማኖት ባለቤት ሆነ፣ የስላሴን ልጅነት አገኘ፣ ወደ አዲስ ህይወት ተሸጋገረ፣ ወዘተ የሚል አስተሳሰብ ያላቸው መሆኑን ነው መረዳት የተቻለው* (ቄስ ባምላኩ ልየው፣ *ቃለ መጠይቅ*፣ 19/03/ 2017 *ዓ.ም*፣ አቃቤት)።

*በተጠኚው ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ እምነት አንድን ህጻን ክርስትና ያነሳ /ች/ የአካባቢው ነዋሪ ካነሳች ዕለት ጀምሮ እስከ ሰባት አመት ድረስ* (አንዳንዶቹ በራስ ፍላጎት ከዚያ በላይ ሊሄዱ ይችላሉ) *ምንም ሳያቋርጡ ከቻሉ ልብስ ጭምር ካልሆነ ግን ከነሃሴ አንድ እስከ አስራ ስድስት* (በፍልሰታ *ጾም ጊዜ*) *ባለው ወቅት ቢያንስ አንድ ህብስት ዳቦ ተይዞ ተሄዶ የክርስትና ልጅን*

መጠየቅ ግዴታ መሆኑን ነው ማረጋገጥ የተቻለው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከሚወልዷቸው ልጆች ሳይለዩ (ወልደውም ከሆነ በተመሳሳይ) በሁሉም ነገር እንደ ልጆቻቸው ሁሉ ለመንከባከብና ለመጠየቅ ቃል የሚገባበት ቀን መሆኑን ነው የጥናቱ መረጃ የሚያሳየው፡፡ ይህን በማድረጉም አንድ የክርስትና አባት (እናት) የነበረ ሰው በአፀደ ስጋ እያለ በሰራው ኃጢያት ሲኦል ከገባ በስቃይ ላይ የሚቆየው የእሱ ክርስትና ልጅ የነበረ ሰው እስከሚሞት ድረስ ብቻ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ምክንያቱም በአካባቢው ማህበረሰብ እምነት በሰማይ ቤት ሁሉም የሞተ ሰው በአካለ ነፍስ ይገናኛል ተብሎ ስለሚታመን የክርስትና ልጁ ነፍስ የክርስትና አባቷን (እናቷን) ነፍስ በሲኦል ውስጥ ስትመለከት በቀጥታ በምድር ላይ ሲደረግላት የነበረውን እንክብካቤ ለፈጣሪ በማቅረብ፣ በመናገርና የምስክርነት ቃል በመስጠት ዋስ ጠበቃ ሆና ታስፈታለች ተብሎ በመታኑ ነው፡፡ ይህ የማህበረሰቡ አስተሳሰብና ተግባር ደግሞ የአካባቢውን ማህበረሰብ ለሚቀበለው ኂላፊነት ተጠያቂ መሆንን የሚማሩበት ሁኔታን ከመፍጠር አንጻር የራሱ የሆነ ጠቀሜታ እንደሚኖረው መናገር ይቻላል፡፡

**ማጠቃለያ**

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደጀን ወረዳ አማራ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ሀገረሰባዊ እምነቶችን ፋይዳ መመርመርና ተገቢ ትንተና ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ሀገረሰባዊ እምነቶች የተጠኘውን ማህበረሰብ ጤናማና አምራች ዜጋ እንዲሆን በማስቻል፣ ሃይማኖቱን የሚያከብር፣ ለሃይማኖቱ ህግና ዶግማው የሚታዘዝ እንዲሆን ከማድረግ አንጻር ፋይዳቸው ቀላል አለመሆኑን ጥናቱ አመላክቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተጠኘው አካባቢ በደን እንዲሸፈንና የተሻለ አካባቢያዊ ስነ-ምህዳር እንዲፈጠር በማድረግ፣ የማህበረሰቡ አባላት በመልካም ስብዕና የተቀረጹ እንዲሆኑ በማስቻል፣ የማህበረሰቡን ኢኮኖሚ ከብክነትና ከጉዳት በመጠበቅ የተሻለ ውጤት እንዲኖረው በማገዝ ረገድ ያላቸው አስተዋጽኦ ቀላል አለመሆኑን አሳይቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በነዋሪዎች መካከል የሚኖረው ማህበራዊ ትስስርና አንድነት ጠንካራ እንዲሆን በማድረግ፣ ምንም እንኳን የባህል መለወጥን ማስቀምም ሆነ መግታት የማይቻል ቢሆንም ነገር ግን በተቻለ አቅም በአካባቢው ያለው ባህል በሌሎች አዳዲስ መጤ ባህሎች እንዳይበረዙና እንዳይተኩ ለመከላከልና ለማስቀጠል እንደ መሳሪያ በመሆን ከማገልገል አኳያ ሚናቸው የጎላ መሆኑን ነው ጥናቱ የሚጠቁመው፡፡

እንዲሁም የማህበረሰቡ አባለት ችግርን፣ መከራንና ክፉ ጊዜን ተቋቁመው ማለፍ የሚችሉ ጠንካራ ስብዕና ያላቸው ሰዎች እንዲሆኑ ከማድረግ አንጻር፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የሴትና የወንድ የስራ ድርሻ ለይቶ ከማሳወቅና ከማስተማር አንጻር አበርክቷቸው ከፍተኛ መሆኑን ነው ከጥናቱ ውጤት መረዳት የሚቻለው፡፡

በመጨረሻም በማህበረሰቡ መካከል ታማኝነት እንዲጠነክር በማድረግ፣ ለሳይንስና ቴክኖሎጅ እድገትና ሽግግር እንደ መነሻ መሰረት ሆኖ በማገልገል፣ በማህበረሰቡ አባላት መካከል ግልጸኝነት፣ መከባበርና ተጠያቂነት እንዲዳብርና እንዲጎለብት ከማድረግ አንጻር ያላቸው ጠቀሜታ ቀላል አለመሆኑን ጥናቱ አሳይቷል፡፡

**የጥቅም ግጭት፡-**ይህ ጥናት ከማንኛውም የጥቅም ግጭት ነጻ ነው፡፡
**የገንዘብ ድጋፍ፡-**ይህ ጥናት የተካሄደው በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲውን አመሰግናለሁ፡፡
**ምስጋና፡-**ይህ ጥናት ለዚህ ደረጃ እንዲደርስ ሙሉ እገዛ ላደረጋችሁልኝ መረጃ አቀባዮችና ተቋማት፤ እንዲሁም ገንቢ አስተያየት ለሰጣችሁኝ አማካሪዎቼ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

**ዋቢዎች**

መኮንን ለገሰ፡፡ 1982 ዓ.ም፡፡ ‹‹የአቴቴ ፈጫሳ ክዋኔና ስነቃላዊ ግጥሞች በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ፡፡›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለቢ. ኤ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

መኮንን በቀለ፡፡ 1973 ዓ.ም፡፡ ‹‹በአማርኛ የሚነገሩ አምልኳዊ ዕምነቶች፡፡›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለቢ. ኤ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ፡፡ 1954 ዓ.ም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት፡፡ አዲስ አበባ፣ በብረሃንና ሰላም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ታተመ፡፡

ሙሉቀን ዘውዱ፡፡ 2001 ዓ.ም፡፡ ‹‹በባህር ዳር አካባቢ በወንዞች ዳር የሚፈጸሙ የአምልኮ ስረዓቶችና ክዋኔያቸው፡፡›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአማርኛ

ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለቢ. ኤ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

ማሞ ተፈራ፡፡ 2002 ዓ.ም፡፡ ‹‹በመኸር ወቅት የሚፈጸሙ ሀገረሰባዊ እምነቶች ፋይዳና የቃል ግጥሞች ይዘት ትንተና፡፡›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለቢ. ኤ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

ሞላ ጀምበሬ፡፡ 2007 ዓ.ም ‹‹የነውር እሳቤ በሊሞ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ እምነት፡፡›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለፎክሎር የፒ. ኤች. ዲ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

ሰሎሞን ተሾመ፡፡ 2007 ዓ.ም፡፡ ፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ፡፡ አዲስ አበባ፣ ፋሪ ኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ.የግ. ማ፡፡

ነጻነት ሰጠኝ፡፡ 1996 ዓ.ም፡፡ ‹‹በደብረዘይት ከተማ በጎዴት ገበሬ ማህበር በወራአና ገልማ ውስጥ የሚከበሩ ዕምነታዊ ስረዓቶች፡፡›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለቢ. ኤ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

አይናዲስ ፍሬው፡፡ 2013 ዓ.ም፡፡ ‹‹የጋብቻ ነውሮች በዳንግላ ወረዳ፡፡›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለፎክሎር ለኤም. ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

ኮማንደር መሃመድ፡፡ 2005 ዓ.ም፡፡ ‹‹የበሪ ሀገረሰባዊ ዕምነት በደቡብ አሪ ወረዳ በምባመር አካባቢ፡፡›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለፎክሎር ለኤም. ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

ዋልተንጉስ መኮንን፡፡ 2007 ዓ.ም፡፡ ‹‹ተፈጥሮን መናቅና ሥጋን ማክበር ለክፉ ዐይን አጋላጭ ክስተት፤ በምስራቅ ጎጃም በሚገኘው የጎዛምን ማህበረሰብ እምነት›› አዲስ አበባ

ዩኒቨርሲቲ፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለፎክሎር የፒ. ኤች. ዲ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡ 1993 ዓ.ም፡፡ ኣማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ግርማ ቡኬ፡፡ 2003 ዓ.ም፡፡ ‹‹የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደርና ዕምነት፡፡›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለፎክሎር ለኤም. ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

ፀዳለ ታደሰ፡፡ 2007 ዓ.ም፡፡ ‹‹በቀይት ንዑስ ወረዳ የሚከወኑ ሀገረሰባዊ እምነቶች፡፡›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለፎክሎር ለኤም. ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ 1991 ዓ.ም፡፡ የስነቃል መምሪያ፡፡ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡

Babamuradova, L. X. (2022). The role of folklore in the moral and aesthetic upbringing of the individual. *World Bulletin of Management and Law, 7*, 72–75.

Barnard, A. (2004). *History and theory in anthropology*. Cambridge University Press. https://doi.org/10.1017/CBO9780511808111

Bascom, W. (1954). Four functions of folklore. *The Journal of American Folklore, 67*(266), 333–349. https://doi.org/10.2307/536411

Bauman, R. (Ed.). (1992). *Folklore, cultural performance, and popular entertainments*. Oxford University Press.

Behailu, G. (1953). Omens in Ethiopia. In A. Pankhurst (Ed.), *Ethnological Society Bulletin* (Vol. 1–10 & Vol. 2, No. 1). Addis Ababa University.

Ben-Amos, D. (1971). Toward a definition of folklore in context. *Journal of American Folklore, 84*(331), 3–15.

Biswas, S., & Bain, K. W. (2022). Conservation of biodiversity using ethnic adaptive folk beliefs: A case study in Purulia district, West Bengal, India. *Antrocom Journal of Anthropology, 18*(1), 45–56.

Dégh, L. (2001). *Legend and belief: Dialectics of a folklore genre*. Indiana University Press.

Dorson, R. M. (Ed.). (1972). *Folklore and folklife: An introduction*. University of Chicago Press.

Dundes, A. (1980). Interpreting folklore. In A. Dundes (Ed.), *Interpreting folklore* (pp. 21–31). Indiana University Press.

Durkheim, É. (1915). *The elementary forms of religious life*. G. Allen & Unwin/Macmillan.

Fetterman, D. M. (2010). *Ethnography: Step-by-step* (3rd ed.). SAGE Publications.

Fiseha, H. (1953). Atete. In A. Pankhurst (Ed.), *Ethnological Society Bulletin* (Vol. 1–10 & Vol. 2, No. 1). Addis Ababa University.

Georges, R. A., & Jones, M. O. (1995). *Folkloristics: An introduction*. Indiana University Press.

Given, L. M. (Ed.). (2008). *The SAGE encyclopedia of qualitative research methods* (Vols. 1–2). SAGE Publications.

Goldstein, K. S. A. (1964). *A guide for field workers in folklore*. Folklore Associates.

Green, T. A. (Ed.). (1997). *Folklore: An encyclopedia of beliefs, customs, tales, music, and art*. ABC-CLIO.

Harmankaya, H., & Atagence, A. (2022). An examination of Turkish folk beliefs concerning clothing: Ankara sample. *Ulakbilge Sosyal Bilimler Dergisi, 10*(77), 456–468. https://doi.org/10.7816/ulakbilge-10-77-04

Heidari, F., Dastgiri, S., Akbari, R., Khamnian, Z., Khanlarzadeh, E., Baradaran, M., Jabbary-Fam, S., Badrazar, S., Heidarzadeh, M., & Tajaddini, N. (2014). Prevalence and risk factors of consanguineous marriage. *European Journal of General Medicine, 11*(2), 83–89. https://doi.org/10.15197/sabad.1.11.81

Kabak, T. (2025). Examination of folk beliefs in Yomra district according to functional theory. REF/JEF (Bucharest), 1-2(2025), 106–120. https://doi.org/10.59277/JEF.2025.12.08

Liu, H. (2023). Guided management of rural folk beliefs under the background of rural revitalization strategy. *Journal of Sociology and Ethnology*, *5*(2), 10–17. https://doi.org/10.23977/jsoce.2023.050210

Louise, H. (2021). The culture: Characteristics and its elements. *Global Journal of Sociology and Anthropology, 10*(3), 1–2.

Malinowski, B. (1944). *A scientific theory of culture and other essays*. University of North Carolina Press.

Malinowski, B. (1948). *Magic, science and religion and other essays*. Beacon Press.

Martha, C. S., & Martine, S. (2011). *Living folklore: An introduction to the study of people and their traditions* (2nd ed.). Utah State University Press.

Mundy-Castle, A., & Bundy, R. (2013). Moral values in Nigeria. *Journal of Cross-Cultural Psychology*.

Murchison, J. M. (2010). *Ethnography essentials: Designing, conducting, and presenting your research*. Jossey-Bass.

O'Connor, B. B. (1995). *Healing traditions: Alternative medicine and the health professions*. University of Pennsylvania Press.

Radcliffe-Brown, A. R. (1952). *Structure and function in primitive society*. Cohen & West.

Sapsford, R., & Jupp, V. (Eds.). (2006). *Data collection and analysis* (2nd ed.). SAGE Publications.

Tripura, M. R. (2025). The impact of migration on the folk beliefs of the tribal people in Tripura: An ethnographic study with special references to Boroks. *International Journal for Multidisciplinary Research, 7*(1).

Turner, J. H., & Maryanski, A. (1979). *Functionalism*. The Benjamin/Cummings Publishing Company.

Yoftahie, K. (1953). Genbot ledata. In A. Pankhurst (Ed.), *Ethnological Society Bulletin* (Vol. 1–10 & Vol. 2, No. 1). Addis Ababa University.